NED

CARD
የመብቶችና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል
Center for Advancement of
Rights and Democracy



# የዩኒቨርሲቲ
## ውስጥ ግጭቶች

በመብቶችና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል የተዘጋጀ

2012 ዓ.ም

# ማውጫ

01 መግቢያ

02 ጥቅል መግቢያ

## መስከረም

## ጥቅምት

05 ወልዲያ ዩኒቨርሲቲ

09 ጂንካ ዩኒቨርሲቲ

## ሕዳር

11 ጅማ ዩኒቨርሲቲ

13 ደንቢዶሎ ዩኒቨርሲቲ

14 አምቦ ዩኒቨርሲቲ

16 ወሎ የኒቨርሲቲ

17 አሶሳ ዩኒቨርሲቲ

18 ወለጋ ዩኒቨርሲቲ

19 መቱ ዩኒቨርሲቲ

20 ደብረታቦር ዩኒቨርሲቲ

21 ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ

22 አዲስ አበባ

23 ጎንደር ዩኒቨርሲቲ

25 መደወላቡ ዩኒቨርሲቲ

26 ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ

27 ባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ

28 ኦዳ ቡልቱ ዩኒቨርሲቲ

28 አርሲ ዩኒቨርሲቲ

29 ደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ

## ታኅሣሥ

31 አምቦ ዩኒቨርሲቲ

32 ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ

33 አምቦ ዩኒቨርሲቲ

35 ወሎ ዩኒቨርሲቲ

36 ሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ

## ጥር

38 ቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ

39 ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ

## የካቲት

41 ወሎ ዩኒቨርሲቲ

42 የተሰወሩት ተማሪዎች እንቆቅልሽ

47 ማጠቃለያ

50 ጥቆማዎች

# መግቢያ

ዩኒቨርሲቲዎች ከዕውቀት ባሻገር በሥነ ምግባር የታነፁና ብቁ የሆኑ፣ ለለውጥ ትልቁን ሚና የሚወስዱ ዜጎች መፍለቂያ ተቋም ቢሆኑም፥ በተቃራኒው የፀብና የግጭት ቦታ ሆነው መታየታቸውም የተለመደ ክስተት ሆኗል። አጠቃላይ በኢትዮጵያ ከሚገኙ 45 ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ አብዛኞቹ በሚባል ሁኔታ ከተመሠረቱበት ዓላማ ውጪ የሆኑ አመፅ አዘል ግጭቶችን አስተናግደዋል።

ይህ መግለጫ በኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች ከመስከረም 2012 ዓ.ም ጀምሮ በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት ትምህርት ቤቶች እስከተዘጉበት ጊዜ ድረስ የተከሰቱ ግጭቶችን ለመዳሰስ ሞክሯል። መረጃዎቹን ለማግኘት ዩኒቨርሲቲዎች ያወጡትን መግለጫ፣ የሚመለከታቸው አካላት የሰጡትን ቃለ መጠይቆች እንዲሁም በተለያዩ የግልና የመንግሥት የዜና አውታሮች የቀረቡ ዘገባዎችን ተመልክቷል።

ይሁን እንጂ ስለ ብዙዎቹ ግጭቶች የሚሰጡ መግለጫዎች፣ ቃለ መጠይቆችና የሚቀርቡ ዘገባዎች በአብዛኛው ብዥታን የሚፈጥሩ፣ ግልጽ ያልሆኑና ለአንድ ወገን ያደሉ፣ በአንዳንድ ዩኒቨርሲቲዎች የተፈጠሩ ችግሮችን አስመልክቶ ደግሞ ጥቂት የሚዲያ ሽፋን ብቻ የተሰጣቸው በመሆኑ፣ ግልጽና በቂ መረጃን የማግኘት ሒደቱን አስቸጋሪ አድርገውት ነበር። ስለዚህም የጠራ እውነታን ለማግኘት ባይቻልም በተቻለ መጠን በአንፃራዊነት ተአማኒነት ያላቸውን ምንጮች በመጠቀም መግለጫው ተዘጋጅቷል።
ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ግጭቶች በተከሰቱ ቁጥር የተጣሩ መረጃዎችን ለሕዝብ ያለመታከት ለማድረስ የሚጥሩ ብዙኀን መገናኛ ድርጅቶችን በተለይም ደግሞ በቴሌግራም ቻናል የተማሪዎችን ድምፅ ለማሰማት ጥረት ያደረጉ የቲክቫሕ-ኢትዮጵያ ቤተሰብ አባላትን እናመሰግናለን። ያለ እነርሱ መረጃዎች ይህ መግለጫ መዘጋጀት አይችልም ነበር።

# ጥቅል መግቢያ

በ2012 ከተዘገቡ እና ከቀላል እስከ ከባድ ግጭቶችን ካስተናገዱ 28 ዩኒቨርስቲዎች በተገኘው መረጃ መሠረት፣ በርካታ የነፍስ መጥፋት፣ ቀላል እና ከባድ አካላዊ ጉዳቶች ተከስተዋል። በእርምት እርምጃም በርካታ ተማሪዎችና ሠራተኞች ከትምህርትና የሥራ ገበታቸው ታግደዋል። የሚከተለው ማጠቃለያ የመግለጫውን ይዘት በጥቅሉ ያሳያል።

## የደረሱ ጉዳቶች

- 12 ተማሪዎች ተገድለዋል፣
- ከ58 በላይ ተማሪዎች ቀላል እና ከባድ ጉዳት ደርሶባቸዋል
- 28 ዩኒቨርሲቲዎች ከመጠነኛ አለመረጋጋት እስከ ከፍተኛ የሆኑ ግጭቶችን በዓመቱ አስተናግደዋል
- ወሎ ዩኒቨርሲቲ 3 ግጭቶች ተከስተውበታል
- ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ በዓመቱ ውስጥ በከፍተኛ ሁኔታ የትምህርት ስርዓቱ ተስተጓጉሏል።
- በሕዳር ወር ብዙ ዩኒቨርስቲዎች (16 ዩኒቨርሲቲዎች) ግጭቶች ተከስተውባቸዋል፤ ሌሎችም ስጋት አንዣበባቸው ከርሟል። የአብዛኛዎቹ መነሻ የጥቅምት ወሩ ወልድያ ዩኒቨርሲቲ ግጭት ነው
- ግጭቶች በምንም ሁኔታ ከተነሱ የብሔር ግጭት ተደርገው ይሳላሉ፣ ወይም ይባዛሉ፤ በዚህም ምክንያት:
    - ከግጭቶች በኋላ ተማሪዎች የደኅንነት ስጋት ስለሚሰማቸው ትምህርት አቋርጠው ወደ ቤተሰባቸው ይመለሳሉ፣ አሊያም ቤተ እምነቶች ውስጥ ተጠልለው ይቆያሉ
    - ማኅበራዊ ሚዲያዎች ግጭቶች ከተከሰቱ በኋላ ከፍተኛ የማቀጣጠል እና የማባባስ ሥራዎች ይከናወኑባቸዋል

## ለግጭቶቹ የእርምት እርምጃ

- 15 ተማሪዎች እና 2 የአስተዳደር ሠራተኞች በግድያ/ሙከራ ተጠርጥረው ታስረዋል/ተከሰዋል[1]
- 3 ምክትል የዩኒቨርሲቲ ፕሬዘዳንቶች፣ 4 መምህራን እና 25 የአስተዳደር ሠራተኞች፣ አንድ የጤና ባለሙያ ከሥራ ታግደዋል/ተሰናብተዋል[2]
- ከ239 ተማሪዎች በላይ በጊዜያዊነት ወይም ሙሉ ለሙሉ ከትምህርት ታግደዋል[3]
- 45 የከፍተኛ ተቋማት ግቢዎች የሰዓት እላፊዎች ጥለዋል
- በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ የደኅንነት ካሜራዎች ተገጥመዋል

1 ይህ ቁጥር የሚያመለክተው በይፋ የተገለጹትን ብቻ ነው። አንዳንድ ዩኒቨርሲቲዎች በተማሪዎች፣ መምህራንና አስተዳደር ሠራተኞች ላይ እርምጃ መወሰዱን ብቻ ያለ ምንም ዝርዝር ስለሚገልጹ እነዚህኞቹ አልተካተቱም።
2 የከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር እርምጃ የተወሰደባቸው መምህራንን ቁጥር 41፣ የአስተዳደር ሠራተኞችን ቁጥር ደግሞ 240 ነው የሚል መግለጫ አውጥቷል። ከላይ የገለጽነው በየዩኒቨርሲቲዎቹ የተገኘውን ግልጽ ዝርዝር ነው።
3 የከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ከአንድ ዓመት እስከናካቴው ከትምህርት ገበታቸው የታገዱት ተማሪዎች ቁጥር 640 ነው ብሏል።

# መስከረም

ወርሐ መስከረም የዩኒቨርስቲ መግቢያ ነጥብ የታወቀበት፣ የአዲስና ነባር ተማሪዎች መግቢያ ቀናት ይፋ የተደረጉበት፣ እንዲሁም ዩኒቨርሲቲ ከሚገቡ ተማሪዎችና ወላጆቻቸው ጋር የሦስትዮሽ የውል ሥምምነት የተፈፀመበት ወቅት ነበር። በመሆኑም በአብዛኛው ዩኒቨርሲቲዎች ያልተከፈቱበትና ትምህርት ያልተጀመረበት ወቅት በመሆኑ ሪፖርት የተደረጉ ግጭቶች አልነበሩም።

# ጥቅምት

በወርሀ ጥቅምት በተለያዩ የሀገሪቱ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ግጭት የተነሳ ሲሆን የተተነሱትን ግጭቶች ያስከተሉትን ጉዳት እና የተወሰደውን እርምጃ በዚህ መልኩ አስቀምጠነዋል።

# ወልዲያ ዩኒቨርሲቲ

በ2012 በኢትዮጵያ ከሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች የመጀመሪያውን ግጭት ያስተናገደው ወልዲያ ዩኒቨርሲቲ ሲሆን በተመሳሳይ ሳምንት በአንዳንድ ዩኒቨርሲቲዎች ለተፈጠሩ ችግሮችም በር ከፋች ሆኖ ነበር። በጥቅምት 29 ቀን በዩኒቨርሲቲው ስለተፈጠረው ሁኔታ ከግምት በዘለለ በእርግጠኝነት የተቀመጠ ነገር ባለመኖሩ የተፈጠረው ሁኔታ ምን እንደነበር፣ መነሻ ምክንያቱና የደረሰው ጉዳትስ ምን ነበር የሚለውን አስመልክቶ የቀረቡ የተለያዩ መረጃዎችን ሚዛናዊ በሆነ መንገድ እንደሚከተለው ለማስቀመጥ ተሞክሯል።

- የአማራ ክልላዊ ብሔራዊ መንግሥት ጉዳዮች ጽሕፈት ቤት ዋና ዳይሬክተር ጌትነት ይርሳው ለክልሉ ቴሌቪዥን ጣቢያ በሰጡት መግለጫ በዩኒቨርሲቲው ከምሽቱ 5፡00 ላይ የተፈጠረው ግጭት ከግምት ውጪ በሆነ ሁኔታ የተከሰተና ምክንያቱ በውል የታወቀ አለመሆኑን ገልፀው፣ ተማሪዎች ኳስ ሲመለከቱ ካመሹ በኋላ ባልታሰበ መንገድ ድንገት የተከሰተ ነው ብለዋል። ግጭቱ የብሔር መልክ እንዲይዝ የሚያደርጉ መረጃዎችንም ነቅፈዋል።[1]
- በሌላ በኩል የወልዲያ ዩኒቨርሲቲ የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር አቶ ተፈራ አስናቀ ለዶይቼ ቬለ (DW) በስልክ በሰጡት ቃለ-መጠይቅ ተማሪዎቹ ቀደም ሲል በአንበጣ መከላከል ሥራ ተጠምደው እንደዋሉና መነሻ ምክንያት የሚመስል ሁኔታ አስቀድሞ አለመታየቱን አስረድተዋል። ለግጭቱ መንስዔ ናቸው ተብለው የሚጠቀሱትንም እንዲህ በማለት ገልፀዋቸዋል፡ "ተማሪዎቹ ሕንፃ ቁጥር 7 ላይ ግጭቱ እንደተነሳ የሚናገሩበት ሁኔታ አለ። በሌላ በኩል የአውሮፓ ሊጎች የእግር ኳስ ጨዋታ ምሽት ነበረ። እዚያ ኳስ ሲመለከቱ፣ ከDSTV አምሽተው ሲወጡ፣ 'ችግሩ እዚያ ነው የተነሳው፣ ከዚያ ጠንከር ብሎ ነው ወደ ዶርም የገባው' የሚሉም አሉ… "ይህን ግጭት የሚፈልጉት ኃይሎች ስላሉ ወዲያውኑ የብሔር ግጭት አደረጉት። በግጭቱ ተማሪዎች፤ ወጣቶች ተጎዱ"።[2]
- የወልዲያ ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዝዳንት አስረስ ንጉሥ (ዶ/ር) "ምሽትአካባቢ የተፈጠረው ችግር ምንጩ እስከሚጣራ ድረስ ከመገመት የዘለለ በትክክል አይታወቅም" ያሉ ሲሆን "በዩኒቨርሲቲው ግቢ ውስጥ ሃይማኖትን በመስበክ እና ወደ ግጭት የሚመሩ እንቅስቃሴዎችን ሲያካሄዱ የነበሩ ተማሪዎች በሥነ ምግባር ግድፈት መታገዳቸውንና በሰሞኑ በአገሪቱ የነበረው የፖለቲካ ችግር መነሻ እንደሚሆን እንገምታለን" ሲሉም ገልጸዋል።[3]

1 አማራ ኮሙኒኬሽን:(ጥቅምት 30) www.facebook.com/AmharaCommunications፣ /ሰኔ 2/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/
2 ዶቸ ቬለ አማርኛ፡ (ሕዳር 30)https://www.dw.com/am/፣ /ሰኔ 2 ቀን ተጎበኘ/
3 የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት(ኢቢሲ) (ጥቅምት 30)፡ www.facebook.com/EBCzena /ሰኔ 2 ቀን ተጎበኘ/

# ወልዲያ ዩኒቨርሲቲ

- አቢኤን የኦሮምኛ ክፍል (OBN) ሁኔታውን 'ጥቃት' በማለት የዘገበው ሲሆን ከለሊቱ 6 ሰዓት እስከ 9 ሰዓት የቆየው ይህ ጥቃት ማንነታቸው ባልታወቁ አካላት ብሔርን ተኮር ባደረገ መንገድ በየዶርሙ በመዞርና በመስበር የተማሪዎችን መታወቂያ በማየት በኦሮሚያ ተማሪዎች ላይ ሆን ተብሎ የተፈፀመ መሆኑን አነጋገርኳቸው ካላቸው ተማሪዎች ያገኘውን መረጃ በገጹ ላይ አስፍሯል።
- በተቃራኒው ይህ ግጭት ቀደም ብሎ የታሰበበትና ቅድመ-ዝግጅት የተደረገበት መሆኑን አንዲት የዩኒቨርስቲው ተማሪ ለአዲስ ማለዳ እንዲህ በማለት አስረድታለች፡- ግጭቱ ቅዳሜ ሊከሰት ሰኞ ላይ 'ቅዳሜ ረብሻ ስላለ የትምህርት ማስረጃችሁን አውጡ' የሚል መልዕክት እንደደረሳቸው፣ የግቢው ድባብና ሳምንቱን ሙሉ የነበረው ሁኔታ ያስታውቅ እንደነበር እና ባለፈው ዓመት ችግር ተፈጥሮ እንደነበርና ዘንድሮም እንደሚነሳ ከነሱ ቀድመው የነበሩ ተማሪዎች እንደነገሯቸው እና ከግቢው ውጪ የገቡ ሰዎች አሉ ሲባልም እንደሰማች ተናግራለች። ግጭቱ የተከሰተ ዕለት ተመራቂ ተማሪዎች ክብ ሠርተው ሲጨፍሩ እንደዋሉ የሚገልጸው ሌላው የአዲስ ማለዳ ምንጭ፣ ውጤታቸው የተበላሸባቸው ተማሪዎች ግጭቱን ቀስቅሰዋል ሲባል መስማቱንም ይናገራል።[1]

የኦሮሚያ ክልል ምክትል ፕሬዝደንት አቶ ሽመልስ አብዲሳ ግጭቱን አስመልክቶ በጽሁፍ በሰጡት መግለጫ፤ "አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች በአቋራጭ ስልጣን ለመያዝ እና አስተሳሰቦቻቸውን በኃይል ህዝብ ላይ ለመጫን ጥረት እያደረጉ ነው" በማለት የተፈጠረውን ሁኔታ ገልፀውታል።[2]

## የደረሱ ጉዳቶች

- 2 የሶሻል ሳይንስ የመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎች ሞት
- 13 ተማሪዎች ቀላልና ከባድ የአካል ጉዳት (የኢፌዴሪ ሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር)
- 4 ተማሪዎች የአካል ጉዳት እንዲሁም አፈና (የኦሮሞ ብሮድካስት ኔትዎርክ)

1 አዲስ ማለዳ (ታህሳስ 8)፡ www.addismaleda.com፣ /ሰኔ 2 ቀን ተጎበኘ/
2 ቢቢሲ አማርኛ(ሕዳር 1)፡ www.bbc.com/amharic፣ /ሰኔ 2 ቀን ተጎበኘ/

# ወልዲያ ዩኒቨርሲቲ

## ቀጣይ ሁኔታዎች

"እኛ ያለንበትን ሁኔታ ሚዲያው በግልጽ አይናገርም፣ እስከመቼ በፀጥታ ኃይሎች እየተጠበቅን በስጋት እናድራለን?" ያሉት የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች፣ ሚዲያዎች ያሉበትን ሁኔታ በግልጽ እያሰሙላቸው እንዳልሆነ ቅሬታቸውን አሰምተው ነበር።[1]

ዩኒቨርሲቲው በሕዳር 7 ቀን ባወጣው ማስታወቂያ የተፈጠረው አለመረጋጋት መሻሻል እየታየበት በመሆኑና አብዛኞቹ ተማሪዎችም ለመማር ፍላጎት በማሳየታቸው እንዲሁም በቂ ጥበቃ በግቢው ውስጥ እየተደረገ በመሆኑ ተማሪዎች ትምህርታቸውን እንዲጀምሩ ለሕዳር 8 ጥሪ አድርጎ የነበረ ቢሆንም የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ግን ከዚህ በተለየ መልኩ ይህን ብለው ነበር:

*"እኛ ሜዳ ላይ ወድቀን 'ትምህርት ተጀምሯል ነገ ሊጀመር ነው' እየተባለ በሚዲያው የሚደሰኮረው ዲስኩር አበሳጭቶናል፤ እኛ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ እያለን ትምህርት ጀምሩ መባሉ ተገቢ አይደለም። ለጥያቄያችን መልስ ይሰጠን (ወደ ቤተሰቦቻችን መሔድ እንፈልጋለን)ከተለያዩ አካላት ጋር ውይይት ቢደረግም መሥማማት ላይ ልንደርስ አልቻልንም"።[2]*

ትምህርት ይጀመርበታል በተባለው በሕዳር 8 ቀን ግን ከኦሮሚያ ክልል የሔዱ በርካታ ተማሪዎች 'ወደ መጣንበት እንመለስ' በማለት የተቃውሞ ድምፅ አሰምተው ነበር። ከፌደራልም፣ ከኦሮሚያና ከአማራ ክልል የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ጋር ውይይት አድርገው ወደ ቀያቸው መመለስ እንደሌለባቸው፣ ይልቁንም ትምህርታቸውን መቀጠል እንዳለባቸው ተገልጾላቸው የነበረ ቢሆንም፥ ከስጋት መውጣት አልቻሉም ነበር። ተማሪዎቹ እንደሚሉት ለደኅንነታቸው ስለሚሰጉ አንድ አዳራሽ ውስጥ ተሰባስበው ለማደር ተገደዋል፤ እንቅስቃሴያቸው በመገደቡም ለተለያዩ አገልግሎቶች ችግር ተጋልጠዋል።[3]

በጥር 6 ቀን ደግሞ ዩኒቨርሲቲው ወደየቤታቸው የሔዱ ተማሪዎች ወደ ግቢ ተመልሰው ትምህርት እንደተጀመረና ማካካሻ ትምህርት እየሰጡ መሆናቸውን አስታውቀው፣ ቁጥራቸው 1500 የሚሆኑ ተማሪዎች ግን አሁንም እንዳልተመለሱ በመግለጽ ትምህርት እንዲጀምሩ ጥሪ አቅርበው ነበር።[4]

በመጋቢት 4 ቀን 2012 አስተማማኝ ሰላም መስፈኑንና የተረጋጋ የትምህርት ስርዓት እያካሔደ መሆኑ ተገልጿል።[5]

1 ቲክቫህ ኢትዮጵያ ቴሌግራም ቻናል (ሕዳር 5)፣/ሰኔ 2 ቀን ተጎበኘ/
2 ቲክቫህ (ሕዳር 7)፣ / ሰኔ 2 ቀን ተጎበኘ/
3 ቢቢሲ አማርኛ(ሕዳር 8)፡ www.bbc.com/amharic፡/ሰኔ 2/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/
4 VOA(ጥር 14): www.amharic.voanews.com፡ /ሰኔ 2/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/
5VOA(መጋቢት 4)፡ www.amharic.voanews.com ፣/ሰኔ 2/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/

# ወልዲያ ዩኒቨርሲቲ



ወደ ዶርምተሪያቸው መመለስ የፈሩ የኒቨርሲቲ ተማሪዎች አንድ ቦታ ተሰብስበው ሲተኙ

## የእርምት እርምጃ

በጥር 8 ቀን የዩኒቨርሲቲው ሴኔት ባስተላለፈው ውሳኔ መሰረት 3 ምክትል ፕሬዝዳንቶቹ ከሥራ ታግደዋል።[1]

ቅዳሜ ጥቅምት 29 በወልዲያ ዩኒቨርሲቲ ይህ ችግር ከተከሰተ በኋላ በአንዳንድ ዩኒቨርሲቲዎች በተለይም የጅማ፣ መደ ወላቡ፣ ሀሮማያ፣ ደምቢ ዶሎ፣ መቱ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የሚታየው ሁኔታ ጥሩ ያልሆነና እንቅልፍ የሚነሳ መሆኑን 'ለቲክቫህ ኢትዮጵያ' ቴሌግራም ቻናል ገልጸው ነበር። በማኅበራዊ ሚዲያ የሚሰራጨው መረጃ፣ ማን እንደሆኑ በማይታወቁ ግለሰቦች በዩኒቨርስቲው ግድግዳ ላይ የሚለጠፉ ማስፈራሪያ ያዘሉ መልዕክቶች ፍርሐት ውስጥ ከተውናል የሚናፈሰው ወሬ እንቅልፍ የሚነሳ ነው፣ በማናውቀው እየተንገላታን በየእምነት ቤቶች ለማደር ተገደናል ማለታቸውን ቲክቫህ ዘግቦት ነበር።[2] ይሁን እንጂ ያንዣበበው ስጋት ቀጥሎ በሕዳር ወር በተለይም በመጀመሪያዎቹ ሳምንታት በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የፀጥታ ችግሮች እንዲከሰቱ ሆኖ ነበር።

1 ኢ.ቢ.ሲ. ዜና(ጥር 9)፣ https://www.facebook.com/EBCzena/posts/3022352991129890፣ /ሰኔ 2/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/
2 ቲክቫህ(ሕዳር 2)፣ /ሰኔ 2/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/

# ጂንካ ዩኒቨርሲቲ

ጥቅምት 30፣ የብሔር ማንነትን መሠረት ያደረገ ግጭት ለመፍጠር በጂንካ ዩኒቨርሲቲ የተደረገ ሙከራ እንደነበር የሚገልጹት የዩኒቨርሲቲው የኮምዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር ዘርጋው ችግሩ የተነሳው ግቢ ውስጥ በተማሪዎች መካከል በሙዚቃ ምርጫ ሳቢያ በተፈጠረ አለመግባባት ነው ብለዋል። ከዚህም በኋላ ተማሪዎች የተቀራረጡ የፌሮ ብረቶችን ወደ ግቢው ይዘው ገብተዋል፤ በመመገቢያ አዳራሽም ለተማሪዎች የተዘጋጁ ምግቦችንም ደፍተዋል ሲሉም አክለዋል።[1]

## የእርምት እርምጃ

በዩኒቨርሲቲው እርምጃ የተወሰደባቸው ተማሪዎች በሚኒ-ሚዲያ ፕሮግራም ላይ ሁከት የፈጠሩ፣ የአካል ጉዳት ወይም ሞትን ሊያስከትል የሚችሉ ፌሮ ብረቶችን ወደ መኝታ ክፍል ያስገቡ፣ መመገቢያ አዳራሽ ምግብ በመድፋት ብጥብጥ ለማስነሳት የሞከሩ እና ብሔር-ተኮር ቅስቀሳ ያደረጉ ናቸው ተብሏል። የተጣለባቸው ቅጣት ሦስት ደረጃዎች አሉት:

- የመጀመሪያ ደረጃ ጥፋተኛ የሆኑትን 5 ተማሪዎች ለሁለት ዓመት ከትምህርት ታግደዋል፣
- በሁለተኛ ደረጃ ጥፋተኛ ሆነው የተገኙ 7 ተማሪዎች ለአንድ ዓመት ከትምህርት ገበታቸው እንዲታገዱ
- በተባባሪነት የተከሰሱ ሌሎች ዘጠኝ ተማሪዎች “ከባድ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ እንዲሰጣቸው” ተወስኗል።

በዩኒቨርሲቲው ውሳኔ ከትምህርት ከታገዱት መካከል ሁለቱ የሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች ሲሆኑ የተቀሩት የመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎች ናቸው። በጂንካ ዩኒቨርሲቲ እርምጃ በተወሰደባቸው ተማሪዎች ሁከት ለመፍጠር ሙከራ ቢደረግም ትምህርት አለመቋረጡን ዘርጋው ጨምረው ገልጸዋል።[2]

1 ጂንካ ዩኒቨርሲቲ (ታህሳስ 16) www.facebook.com፣ /ሰኔ 3/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/
2 ዶቼ ቬለ(ታህሳስ 19): www.dw.com/am፣/ሰኔ 3/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/

# ሕዳር

በወርሀ ሕዳር በተለያዩ የሀገሪቱ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ግጭት የተነሳ ሲሆን የተተነሱትን ግጭቶች ያስከተሉትን ጉዳት እና የተወሰደውን እርምጃ በዚህ መልኩ አስቀምጠነዋል።

# ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## ቀጣይ ሁኔታዎች

በቀጣይ ቀናቶች ዩኒቨርሲቲው ለተፈጠሩ ችግሮች እልባት ለመስጠት የታለመ ውይይት አካሄዶ ነበር። ምዝገባም እንዲካሔድ ከሁለት ሳምንታት በኋላ ጥሪ አቅርቦ፣ ነገር ግን ተማሪዎች እንዳይረጋጉና ምዝገባ አከናውነው ወደ ትምህርት እንዳይመለሱ በማኅበራዊ ሚዲያ የማስፈራሪያ መልዕክቶችን ለማስተላለፍ ሙከራ የሚያደርጉ አካላት መኖራቸውን እንደደረሰበትና ጥብቅ ክትትል እያደረገ መሆኑን ገልጾ ነበር።[1]

'በሌላ በኩል ቲክቫህ የዩኒቨርሲቲውን ተማሪዎች እንዳነጋገረው ከሆነ ተማሪዎች የመማር ፍላጎት ቢኖራቸውም ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በተመሳሳይ መልኩ በዩኒቨርሲቲው ውስጥና በማኅበራዊ ሚዲያ የሚሰራጩ መልዕክቶች ትምህርታቸውን ለመጀመር እንቅፋት እንደሆነባቸው ገልፀዋል።፡ "ከተመዘገባችሁ፣ ትምህርት ከጀመራችሁ እርምጃ እንወስዳለን" የሚሉ መልዕክቶች እንዳይመዘገቡና ትምህርት እንዳይጀምሩ እንዳደረጋቸው ተናግረዋል።[2] ወደቤታቸው ያልሔዱ ተማሪዎችም በየቤተ እምነቱ ተጠልለው ይገኛሉ። "የሚሰማን አጣን፣ ያለንበት ሁኔታ እጅግ የሚያሳዝን ነው። እኛ ወደ ቤት መሔድ ያልቻልን ተማሪዎች ከፍተኛ እንግልት ውስጥ ወድቀናል፤ የሚሰማ አካል ካለ መፍትሔ ይሰጠን" ብለው ነበር። ዩኒቨርሲቲው ደግሞ ወደ ትምህርት ገበታቸው መመለስ የማይፈልጉ በግቢው የሚገኙ ተማሪዎች፣ አስፈላጊውን ፎርማሊቲ አሟልተው ግቢውን ለቀው እንዲወጡ ማሳሰቢያ ሰጥቷል። በዩኒቨርሲቲው ተቋርጦ የነበረው የመማር ማስተማር ሒደት ከሰኞ ታኅሣሥ 20 ቀን 2012 ጀምሮ የቀጠለ ቢሆንም፣ ተማሪዎች በተሟላ ሁኔታ ወደ ትምህርት ገበታቸው ባለመመለሳቸው ምክንያት ወደ ትምህርታቸው መመለስ ለማይፈልጉ ለጅማ ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ተማሪዎች አገልግሎት መስጠት እንደሚያቋርጥና ለቀው እንዲወጡ በጻፈው ደብዳቤ ማሳሰቢያ አስተላልፎ ነበር።[3]

1 ጅማ ዩኒቨርሲቲ (ሕዳር 12) www.facebook.com፣/ሰኔ 4/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/
2 ቲክቫህ (ሕዳር 12)፣ /ሰኔ 4/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/
3 ሪፖርተር(ታህሳስ 26)፡ www.ethiopianreporter.com፡ /ሰኔ 4/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/

# ጅማ ዩኒቨርሲቲ



ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## የእርምት እርምጃ

ታኅሣሥ 30፣ ጅማ ዩኒቨርሲቲ የሚከተሉትን እርምጃዎች ወስዷል:

- 31 ተማሪዎች የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል
- 20 ተማሪዎች ከ1 ዓመት እስከ ሙሉ በሙሉ ከትምህርት ታግደዋል
- ከተቋማዊ ለዉጥ ሒደቱ ጋር በተገናኘ በአስተዳደርና ተማሪዎች አገልግሎት ዘርፍ የምክትል ፕሬዝዳንት እና የ3 ዳይሬክተሮች እንዲሁም በሌሎች ዘርፎችም የ3 ሃላፊዎች ለውጥ አድርጓል።
- በሌላ በኩል የደኅንነት ካሜራ በመግቢያና መውጫ በር ላይ መግጠሙ ታውቋል

የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች በመግቢያና መውጫቸው ላይ የደኅንነት ካሜራ እንዲገጥሙ አዞ የነበረ ሲሆን አዲስ አበባ፣ ጎንደር፣ ጅማ፣ ሐዋሳ፣ ዋቻሞ ዩኒቨርሲቲዎች ደግሞ በራሳቸው ተነሳሽነት የደኅንነት ካሜራ ገጥመዋል።[1]

1 ቲክቫህ(ጥር 8) ፤/ሰኔ 7/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/

# ደንቢዶሎ ዩኒቨርሲቲ



በተመሳሳይ በሕዳር 01 በደንቢዶሎ ዩኒቨርሲቲ ምሽት አካባቢ በተማሪዎች መመገቢያ አዳራሽ ውስጥ አለመረጋጋት ተፈጥሮ ነበር። የዩኒቨርሲቲው የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር ተመስገን ዓለሙ ለዶይቼ ቬለ እንደገለጹት፡-

*"...ጊቢው በሙሉ በተጠንቀቅ ነበር። ወሊጋ በአጠቃላይ ኮማንድ ፖስት ስር ስለሆነ ያለው፤ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የፌዴራልም፣ የመከላከያም፣ የኦሮሚያም የፀጥታ ኃይሎች ነበሩ። ነገሩ አልታሰበም ሰላማዊ ነበር አካባቢው፤ በማይታሰብ ሁኔታ ነው ያ ነገር የተከሰተው። የተማሪዎች የመመገቢያ አዳራሽ አካባቢ ነው ችግሩ የተፈጠረው።"*[1]

## የደረሱ ጉዳቶች

- የ1 ተማሪ ሞት
- ትምህርት ለጊዜው ተቋርጦ ነበር
- ቁጥራቸው ያልታወቀ ተማሪዎች ቀላልና ከባድ የአካል ጉዳት
- የተወሰኑ ተማሪዎች ከግቢው በመውጣት በእምነት ተቋማት ተጠልለው ነበር
- 3 ተማሪዎች ታፍነው ተወስደዋል (አስራት ቴሌቪዥን)[2]

## ቀጣይ ሁኔታዎች

"ዛሬም የፀጥታ ስጋት አለብን" በማለት በማግስቱ አስራት ቴሌቪዥን ያናገራቸው ተማሪዎች ተናግረው ነበር።[3] በየኒቨርሲቲው ውስጥ ካሉ ከፍተኛ ሥራ አመራሮች፣ ተማሪዎች እና ከአገር ሽማግሌዎች ጋር ውይይት ተደርጓል። ነገር ግን የትምህርት ስርዓቱ በተደጋጋሚ በመቋረጡ ምክንያት ዩኒቨርሲቲው ለሦስተኛ ጊዜ ትምህርት ያቋረጡ የደምቢዶሎ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ትምህርታቸውን መቀጠል የማይችሉ ከሆነ፣ ላልተወሰነ ጊዜ እንደሚዘጋ ዩኒቨርሲቲው አስታወቆ ነበር። ተማሪዎች ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ የተለያዩ የማግባባት ሥራዎች ቢከናወኑም፣ አለመሳካታቸውንና በመሆኑም በፍጥነት ወደ ትምህርት ገበታቸው ካልተመለሱ፣ ላልተወሰነ ጊዜ ሙሉ ለሙሉ እንደሚዘጋ ዩኒቨርሲቲው ይፋ አድርጎ ነበር።[4]

1 ዶቸ ቨለ አማርኛ (ሕዳር 3) : www.dw.com/am
2 አስራት ቴሌቪዥን /ሰኔ 8/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/
3 አስራት ሚዲያ(ሕዳር 2)፡ www.facebook.com/AmharaMassMediaAgencyAMMA ሰኔ 8/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/
4 ሪፖርተር(ታህሳስ 26)፡ www.ethiopianreporter.com/article ፣ /ሰኔ 8/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/

# አምቦ ዩኒቨርሲቲ




አምቦ ዩኒቨርሲቲ

በአምቦ ዩኒቨርሲቲ በሕዳር 3፣ በወልድያ ዩኒቨርሲቲ ግጭት ከተከሰተ በኋላ የተወሰኑ ተማሪዎች ዩኒቨርስቲውን መልቀቅ እንደጀመሩ አንድ የዩኒቨርሲቲው ተማሪ ለዶይቼ ቬለ ተናግሯል።[1] የጥቅምት 29 የወልዲያ ዩኒቨርሲቲን ክስተት ተከትሎ በሕዳር 3 ቀን በዩኒቨርስቲው ጥቂት ተማሪዎች የተቃውሞ ሰልፍ ማድረጋቸውንና ሰልፉ ወደ ግጭት አምርቶ ከአማራ ክልል የመጡ የዩኒቨርስቲው ተማሪዎች ላይ ጉዳት መድረሱን አዲስ ማለዳ ዘግቧል።[2]

## የደረሱ ጉዳቶች

- 10 ተማሪዎች ቀላል ጉዳት ደርሶባቸዋል
- ተማሪዎቹ በእምነት ተቋማት ተጠልለው ነበር
- የትምህርት ሒደቱ ተቋርጦ የተወሰኑት ወደ መጡበት ተመልሰው ነበር

የሳይንስ እና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር የኮሚዩኒኬሽን ዳይሬክተር ደቻሳ ጉርሙ ግን ተማሪዎቹ ከዩኒቨርሲቲው ወጥተው እየሔዱ መሆናቸውን ተጠይቀው ማስተባበላቸውን ዶቼ ቬለ ጠቅሷል[3] የአምቦ ዩኒቨርሲቲ አመራሮች በወቅቱ በቂ ምላሽ ለመስጠት ብዙም ፍቃደኛ እንዳልነበሩ የዶይቼ ቬለ ዘገባ ያሳያል። ስለዚህም ከእነሱ ወገን ያለውን ዝርዝር ለማግኘት አልተቻለም።

1 ዶቸ ቬለ (ሕዳር 8) www.facebook.com/dw.amharic/ሰኔ 8/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/

2 አዲስ ማለዳ(ሕዳር 8)፡ https://addismaleda.com/archives/8197, /ሰኔ 9/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/

3 ibid

# አምቦ ዩኒቨርሲቲ




አምቦ ዩኒቨርሲቲ

## ቀጣይ ሁኔታዎች

በዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ወደ ክፍል ገብተው ለመማር ፈቃደኛ ሳይሆኑ መቅረታቸውንና በግቢዎቹ በፀጥታ አካላት ጥብቅ ጥበቃ እየተደረገ መሆኑን ተማሪዎች አስረድተዋል።[1] ግጭት በተከሰተባቸው ዩኒቨርስቲዎች ከተማሪዎች ጋር ውይይት ተደርጓል ያሉት በሚኒስቴሩ የኮሙኑኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር የሆኑት ደቻሳ ጉርሙ ተማሪዎች ለመማር መወሰናቸውን ገልጸዋል። በአምቦ ዩኒቨርስቲ ተመሳሳይ ውይይት ተደርጎ መግባባት ላይ እንደተደረሰም ለዶይቼ ቬለ አስረድተዋል። አምቦ ዩኒቨርሲቲ ባወጣው ማስታወቂያ በሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች የተፈጠረውን ችግር ተከትሎ የትምህርት ስርዓቱ ተስተጓጉሎ እንደነበር በማስታወስ የፀጥታ ችግሩ ወደ ዩኒቨርሲቲው እንዳይስፋፋ ሲሠራ የቆየ መሆኑንና አሁን ላይ ትምህርት ለማቋረጥ ምክንያት ባለመኖሩ ትምህርት እንዲጀምሩ አሳስቦ ነበር።[2]

1 ቢቢሲ አማርኛ(ሕዳር 3)፡ www.bbc.com/amharic /ሰኔ 9/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/
2 አምቦ ዩኒቨርሲቲ(ሕዳር 8)፡ https://www.facebook.com /ሰኔ 9/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/

# ወሎ ዩኒቨርሲቲ




ወሎ ዩኒቨርሲቲ መግቢያ

በዓመት ውስጥ 3 ግጭቶች የታዩበት ወሎ ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያውን አለመረጋጋት ያስተናገደው በሕዳር 3 ቀን ነበር። ግጭቱ የተፈጠረው በደሴ ግቢ ነበር። ዩኒቨርሲቲው በጊዜው ምክንያቱ ባልታወቀ ምክንያት ችግሩ እንደተነሳ ቢገልጽም ከቀናት በኋላ ግን በማኅበራዊ ሚዲያ የሚሰራጩ የሐሰት መረጃዎችና የፖለቲካ ጥቅመኞች ግፊት መንስዔ ነው ብሏል።[1]

## የደረሱ ጉዳቶች

- የ1 ተማሪ ሞት
- የ1 ተማሪ ከባድ የአካል ጉዳት
- ቁጥራቸው ያልተገለጸ ተማሪዎች ቀላል የአካል ጉዳት

## ቀጣይ ሁኔታዎች

ተማሪዎች እንዳሳወቁት ከሆነ በዩኒቨርሲቲው ተረጋግቷል አልተረጋጋም ለማለት የሚከብድ ሁኔታ ነበር። በወቅቱ ተማሪዎች በጭንቀትና በስጋት ውስጥ ነበሩ ትምህርትም ተቋርጦ መፍትሔ ማግኘት አልቻሉም ነበር።[2]

ችግሩ ከተፈጠረ ዕለት ጀምሮ በየደረጃው በተደረገ ውይይት መግባባት ላይ በመደረሱ ትምህርት በሕዳር 14 ቀን መጀመሩ ተገልጿል።

1 ቲክቫህ (ሕዳር 14), /ሰኔ 9/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/
2 ቲክቫህ ኢትዮጵያ (ሕዳር 10), /ሰኔ 8/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/

# አሶሳ ዩኒቨርሲቲ

ሕዳር 3 በአሶሳ ዩኒቨርሲቲ በተማሪዎች መመገቢያ አዳራሽ እና በሌሎች ቦታዎች የወልዲያ ዩኒቨርሲቲውን ግጭት መነሻ ያደረገ መጠነኛ አለመረጋጋት ተፈጥሮ ነበር።

## የእርምት እርምጃ

አሶሳ ዩኒቨርሲቲ የካቲት 19 ቀን የሚከተሉትን ውሳኔዎች አስተላልፏል፦

- በ22 ተማሪዎች ላይ ከከባድ ማስጠንቀቂያ እስከ ሁለት ዓመት ከትምህርት ማገድ እርምጃ ተወስዷል። እርምጃ ከተወሰደባቸው ተማሪዎች መካከል እስከ ሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች ይገኙበታል። በምርመራው መሠረት ተማሪዎቹ ብጥብጥና ሁከት ለማስነሳት በማደሪያ ቦታ ስለት ያለው መሣሪያ፣ ዱላ እና ፌሮ ብረት ይዘው እንደተገኙ አመልክተዋል። “በዩኒቨርሲቲው መመገቢያ አዳራሽ ለግጭት የሚጋብዙ ድርጊቶችን ፈፅመዋል” ብለዋል።
- አብሮት ሲማር በነበረ ተማሪ ላይ የመግደል ሙከራ ያደረገ አንድ ሌላ ተማሪ ደግሞ በሕግ አስከባሪዎች ተይዞ ጉዳዩ በፍርድ ቤት እየታየ እንደሆነ ረዳት ፕሮፌሰር አበራ አስረድተዋል።
- በዩኒቨርሲቲው የተማሪዎችን ጥያቄዎች አቅም በፈቀደ ምላሽ በመስጠት ችግሮች ሳይከሰቱ አስቀድሞ ለመፍታት ከተማሪዎች እና መምህራን ጋር ተከታታይ ውይይቶች እየተደረጉ መሆናቸውንም ጠቁመዋል። በተለይ የቅሬታ ምንጭ የሆኑ የምግብ፣ መኝታ እና ተያያዥ የተማሪዎችን አገልግሎት የዩኒቨርሲቲው አመራሮች በየጊዜው ድንገተኛ ጉብኝት በማድረግ ለማስተካከል ጥረት እየተደረገ መሆኑን ጠቅሰዋል። ይህ ዘገባ በወጣበት ማለትም በየካቲት 18 ወቅትም በዩኒቨርሲቲው ሰላማዊ የመማር ማስተማር ሥራ መቀጠሉን ገልጸው ነበር።[1]

1 የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ኤጀንሲ (የካቲት 18) ፣www.facebook.com, /ሰኔ 10/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/

# ወለጋ ዩኒቨርሲቲ

የሕዳር 4ቱ አለመጋጋት ከመፈጠሩ አስቀድሞ በወልዲያ ዩኒቨርስቲ በተፈጠረው ነገር ተማሪዎች እጅግ መቆጣታቸውንና በዚህም ምክንያት ሰላማዊ ሠልፍ በማድረግ ድምፃቸውን ማሰማት ቢፈልጉም፥ ነቀምት ከተማ በሚገኘው ኮማንድ ፖስት ምክንያት ባለመቻላቸው ቁጣና ተቃውሟቸውን የረሃብ አድማ በማድረግ መግለጻቸውን የዩኒቨርሲቲው የ3ኛ ዓመት ተማሪ ለቢቢሲ አማርኛ እንዲህ በማለት ገልጿል፤ "ወንድሞቻችን እየሞቱ፣ ወንድሞቻችን እየተቸገሩ እኛ እንዴት ምግብ እንመገባለን ብለን ምሳችን ባለመመገብ ሐዘናችንን ገልጸናል" በማለት ዩኒቨርስቲ ውስጥ በብሔር ምክንያት የተፈጠረ ችግር እንደሌለ ያስረዳል።
በወቅቱም ተማሪዎች ወደ ክፍል ገብተው ለመማር ፈቃደኛ ሳይሆኑ መቅረታቸውንና በግቢዎቹ በፀጥታ አካላት ጥብቅ ጥበቃ እየተደረገ መሆኑን ተማሪዎች አስረድተዋል። የዩኒቨርሲቲው የሁለተኛ ዓመት ተማሪ እንደተናገረው ከሆነ የፀጥታ ኃይሎች በዩኒቨርሲቲው ሕንፃ ላይ ከገቡ በኋላ ተማሪዎች የመረበሽ ስሜት ውስጥ እንዳሉ ያስረዳል። የዩኒቨርስቲው የፀጥታ አስከባሪ አካላትና የተማሪው ቁጥር በአቻነት እንደሚገኝ የሚናገረው ይህ ተማሪ፣ ብዙ ተማሪዎች በፍርሐት ወደ ቤተሰቦቻቸው እየተመለሱ መሆኑን ተናግሯል። ቢቢሲ አማርኛ ያነጋገረው የወለጋ ዩኒቨርስቲ መምህር በበኩሉ፤ ተማሪዎች ላነሱት ቅሬታ ዩኒቨርስቲው የሰጠው መልስ እንደሌለ ገልጾ ትምህርት መቋረጡን አረጋግጧል። "እኛ ለማስተማር ዝግጁ ነን። በየዕለቱ ሥራችን ላይ ብንኖርም አንድ ተማሪ ተረጋግቶ መማር የሚችለው በሥነ ልቦና የተረጋጋ አካባቢና ሁኔታ ውስጥ ሲኖር ነው" ብሏል።[1]
በሕዳር 4 ቀን በወለጋ ዩኒቨርሲቲ ጊምቢ ካምፓስ በተማሪዎች መመገቢያ አካባቢ ችግር ተፈጥሮ የነበረ ሲሆን የግቢው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ዳይሬክተር ቀናቴ ነጋሳ እንደተናገሩትም ጠዋት በተማሪዎች መመገቢያ አካባቢ ተማሪዎች ድንጋይ በመወራወራቸው የተወሰነ ችግሮች ቢፈጠሩም ችግሩን በፀጥታ ኃይሉ ለመቆጣጠር ተችሏል።

1 ቢቢሲ አማርኛ(ሕዳር 3)፡ BBC Amharic: www.bbc.com/amharic ሕዳር 3/2012, /ሰኔ 10/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/

# መቱ ዩኒቨርሲቲ

ብዙም ሽፋን አይሰጠው እንጂ እንደሌሎቹ ዩኒቨርሲቲዎች ሁሉ መቱ ዩኒቨርሲቲም የወልዲያን ክስተት ተከትሎ በሕዳር ወር መጀመሪያዎቹ አካባቢ አለመረጋጋት ተፈጥሮ ነበር።

## የደረሱ ጉዳቶች

- የትምህርት ስርዓቱ ተስተጓጉሏል
- ተማሪዎች በመጠለያዎች ተጠልለው ነበር

## ቀጣይ ሁኔታዎች

ግጭቱን ተከትሎ የዩኒቨርሲቲው ሴኔት በሕዳር 8 ቀን ባስተላለፈው ውሳኔ ከዶርም ወጥተው በአዳራሽ ተጠልለው ያሉ ተማሪዎች ወደተዘጋጀላቸው መኝታ ክፍላቸው እንዲገቡ፣ ተማሪዎች ዳግም ምዝገባ እንዲያካሒዱ፣ መማር የሚፈልጉ ተማሪዎች ከሕዳር 15 ጀምሮ ትምህርታቸውን እንዲጀምሩ የወሰነ ቢሆንም ተማሪዎች ግን ይህንን ቅሬታ አሰምተው ነበር:

*“ዛሬ ወደ ዶርማችሁ ትገባላችሁ የተባለ ቢሆንም ሳንገባ ቀርተናል፤ ችግራችን እስካሁን አልተፈታም። የተማሪዎች ጥያቄ ወደ ቤተሰብ እንመለስ ቢሆንም ዩኒቨርሲቲው እንዳይሔዱ አድርጓል። መንግሥት ይህን ያህል ስንሰቃይ ለምን ዝም እንደሚል ግራ ተጋብተናል።”*

በድጋሚ በሕዳር 12 ቀን ቅሬታቸውን እንደገለጹት ከሆነ ዩኒቨርሲቲው ትምህርት ጀምሩ ሲል በሌላ በኩል ደግሞ የማያውቋቸው አካላት ትምህርት እንዳትጀምሩ እያሉ በማስፈራራት እንደሚለጥፉና ተማሪዎች የትኛውን አምነው መቀበል እንዳለባቸውና ለደኅንነታቸውም ዋስትና እንደሌላቸው፣ ስለዚህም መንግሥት እርምጃ እንዲወስድ በማለት ጠይቀው ነበር።[1]

## የእርምት እርምጃ

የዩኒቨርሲቲው ሴኔት ጥር 6 ቀን 2012 ባካሔደው አስቸኳይ ስብሰባ የመማር ማስተማር ሒደቱን አውከዋል ባሏቸው 26 ተማሪዎች ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ወስዷል።

- በዚህም 12 ተማሪዎች ለሁለት ዓመት፣
- ተማሪዎች ለአንድ ዓመት እንዲሁም

8 ተማሪዎች ሙሉ ለሙሉ ከትምህርት ገበታቸው እንዲታገዱ ውሳኔ አሳልፏል

1 Ibid (ሕዳር 12), /ሰኔ 13/2012 ዓ.ም ተገበኘ/

# ደብረታቦር ዩኒቨርሲቲ




ደብረታቦር የኒቨርሲቲ

በተመሳሳይ ብዙም ሽፋን አይሰጠው እንጂ ደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲም የወልዲያን ክስተት ተከትሎ በሕዳር ወር መጀመሪያዎቹ አካባቢ አለመረጋጋትን አስተናግዶ ነበር።

## የደረሱ ጉዳቶች

- 2 ተማሪዎች ተጎድተው ነበር
- ከሕዳር 4 ቀን ጀምሮ ትምህርት ተቋርጦ ነበር
- በርከት ያሉ ተማሪዎች ግቢውን ለቀው ወጥተዋል

## ቀጣይ ሁኔታዎች

በሕዳር 7 ቀን የዕርቅ ፕሮግራም፣ በሕዳር 8 ቀን ደግሞ የውይይት ፕሮግራም ተዘጋጅቶ ነበር። ተማሪዎች በበኩላቸው ያለንበት ሁኔታ በዩኒቨርሲቲው እንደሚገለጸው አይደለም፣ ስጋታችን አልተቀረፈም ብለዋል። በግቢው ውስጥ በተፈጠረው ችግር ምክንያት ለቀው የሔዱ ተማሪዎች አሉ፤ እኛም የምናድረው የመማሪያ ክፍል ውስጥ ነው ሎከሮቻችን እየተሰበሩ ዝርፍያ ተፈፅሞብናል። ይህንን ግን ግቢው እየገለጸ አይደለም ብለዋል። ዩኒቨርሲቲው በበኩሉ በግጭቱ የተጎዱት ተማሪዎች ሕክምና ተደርጎላቸው በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛሉ ብሏል።[1]

1 ቲክቫህ (ህዳር 7) /ሰኔ 13/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/

# ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ




ድሬዳዋ የኒቨርሲቲ

በግቢው ውስጥ በሕዳር 7 ቀን አለመረጋጋት ተፈጥሮ ነበር። በዚህም አንድ የ3ኛ ዓመት ተማሪ ከፎቅ ወድቆ ህይወቱ አልፏል።[1] ይሁን እንጂ የሕዳር 7ቱ ክስተት ከመፈጠሩ አስቀድሞ በግቢው መመገቢያ ካፌ ውስጥ ምሽት አካባቢ ላይ ግጭት ተፈጥሮ የነበረ ሲሆን በተፈጠረው አለመረጋጋት ሳቢያ በርካታ ተማሪዎች እየተንገላቱ እንደሆነና ግቢው ብቻ ሳይሆን ውጪውም የተረጋጋ ባለመሆኑ ከፍተኛ የደኅንነት ስጋት ስለገባቸው የሚመለከታቸው አካላት ትኩረት እንዲሰጠው በማለት በሕዳር 5 ቀን ለቲክቫህ ገልጸው ነበር።[2]

## የደረሱ ጉዳቶች

- የአንድ የ3ኛ ዓመት ተማሪ ሞት
- ተማሪዎች የግቢውን አጥር እየዘለሉ ወጥተዋል
- በየቤተ እምነቱ ሸሽተው የተቀመጡ ነበሩ
- የትምህርት ስርዓቱ ተስተጓጉሏል

## ቀጣይ ሁኔታዎች

ትምህርት በሕዳር 15 ቀን እንደሚጀመር ቢነገርም የተለያዩ ማስፈራሪያዎች እየተሰራጩ በመሆኑ በርካታ ተማሪዎችም ግቢውን ለቀው ወጥተው ነበር።[3]

1 ቢቢሲ አማርኛ(ሕዳር 8)፡ www.bbc.com/amharic , /ሰኔ 13/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/
2 ቲክቫህ(ሕዳር 5), /ሰኔ 13/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/
3 Ibid ሕዳር 14/2012, /ሰኔ 13/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ



አዲስ አበባ የኒቨርሲቲ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሕዳር 11 ቀን ከቀኑ 7፡30 አካባቢ መጠነኛ አለመረጋጋት ተፈጥሮ ነበር።

## መንስኤ

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ፕሮፌሰር ጣሰው ወልደሀና ግርግሩ ተማሪዎች ባነሱት ጥያቄ የተፈጠረ መሆኑን ገልፀዋል። ጥያቄው ምን ነበር የሚለውን ግን ከመግለፅ ተቆጥበዋል። ከደቂቃዎች በፊትም በራሪ ወረቀቶች ሲበተኑና መፈክሮች ሲሰሙ እንደነበር የአባይ ሚዲያ ዘገባ ያሳያል።[1]

ሁኔታውን የፖሊስ አካላት በግቢው ወስጥ በመግባትና ግቢውን በሮች በመዝጋት ሊያረጋጉት ችለዋል። በወቅቱም ከዚሁ ጉዳይ ጋርም በተያያዘ የፀጥታ አካላት 2 ሰዎችን በቁጥጥር ስር በመዋል ከዩኒቨርሲቲው ይዘው ሲወጡ ታይተዋል።[2]

1 አባይ ሚዲያ(ሕዳር 11)፡ http://amharic.abbaymedia.info/archives/47618, /ሰኔ 13/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/
2 ቲክቫህ(ሕዳር 11), /ሰኔ 13/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/

# ጎንደር ዩኒቨርሲቲ

በጎንደር ዩኒቨርሲቲ ቴዎድሮስ ካምፓስ በሕዳር 29 ቀን ተመሳሳይ ችግር ተፈጥሮ ነበር። የሕዳር 29 ክስተት ከመፈጠሩ ከሳምንት በፊት በዩኒቨርሲቲው የጎላ ችግር ባይኖርም በሚናፈሱ ወሬዎች ስጋት ወደ ቤተሰቦቻቸው የሔዱ ተማሪዎች መኖራቸውንና በግቢው ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ደግሞ ከፍተኛ የደኅንነት ስጋት እንዳለባቸው ተገልጾ ነበር። ትክክለኛ ምክንያቱ ግን በይፋ አልተገለጸም።[1]

ይህ ስጋት ቀጥሎ በሕዳር 29 ቀን 2012 ቀን ንጋት 12 ገደማ በተማሪዎች ሽንት ቤት አካባቢ አንድ የ2ኛ ዓመት ተማሪ በደረሰበት ጉዳት ሕይወቱ አልፏል። የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት አስራት አፀደወይን (ዶ/ር) ለቪኦኤ በስልክ በሰጡት ቃለመጠይቅ ጉዳቱን በማድረስ የተጠረጠሩት ከተማሪው ዶርም ፊት ለፊት የሚኖሩ 2 ተማሪዎች ሲሆኑ፣ በቁጥጥሩ ሥር መዋላቸውን ገልጸዋል።




ጎንደር ዩኒቨርሲቲ

## የደረሱ ጉዳቶች

- የ1 ተማሪ ሞት
- የትምህርት ስርዓት መስተጓጎል

1 ቲክቫህ (ሕዳር 21), /ሰኔ 13/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/

# ጎንደር ዩኒቨርሲቲ

## የእርምት እርምጃ

በታኅሣሥ 22 ቀን ዩኒቨርሲቲው ባሳለፈው ውሳኔ እንደገለፀው:

- 2 ተማሪዎች አንድ ዓመት ከትምህርት ገበታቸው እንዲታገዱ፣
- 39 ተማሪዎች ለሁለት ዓመት ከትምህርት ገበታቸው እንዲታገዱ
- 11 ተማሪዎች ሙሉ በሙሉ ከትምህርት ገበታቸው (ከዩኒቨርሲቲው) እንዲሰናበቱ
- 7 መምህራን ቀላል የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ፣
- ለ3 መምህራን የመጨረሻ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ፣
- ለ3 መምህራን እና ለ8 የአስተዳደር ሰራተኞች እንዲሁም የጤና ባለሙያ ሙሉ በሙሉ ከሥራ እንዲሰናበቱ ተወስኗል።[1]
- የጤና ባለሙያው "የአምቡላንስ አሽከርካሪ ግጭት ሲከሰት በሥራ ገበታው ላይ ባለመገኘቱ፤ ለአንድ ተማሪ ሞት ምክንያት ሆኗል" በሚል ሙሉ ለሙሉ ከሥራው የተሰናበተ ነው
- የጦር መሣሪያ አስቀምጠው የተገኙ ፕሮክተሮችም እርምጃው ከተወሰደባቸው የአስተዳደር ሠራተኞች መካከል ይገኛሉ።
- እርምጃ የተወሰደባቸው "ሁከት የፈጠሩ፣ ያባባሱ፣ ተማሪዎችን የሚስፈራሩ መልዕክቶችን ሲለጥፉ የተያዙ" ናቸው ተብሏል[2]
- 158 የደኅነት ካሜራዎች በአራቱም ጊቢዎች በሚገኙ የምግብ አዳራሾች፣ ቤተ መጽሐፍት፣ በተማሪዎች ማደሪያና የመማሪያ ሕንጻዎች እንዲሁም በዋና ዋና የመግቢያ በሮች ተተክለዋል[3]
- በሕዳር 15 ቀን ትምህርት አንደተጀመረ ተገልፆ የነበረ ቢሆንም፥ በድጋሚ ትምህርት እየተስተጓጎለ በመሆኑ ሁሉም ተማሪዎች ጥር 4 ትምህርት እንዲጀምሩ ጥሪ ቀርቦ ነበር።

1 ጎንደር ዩኒቨርሲቲ(ታህሳስ 22)፡www.facebook.com/TheUniversityofGondar/, /ሰኔ 13/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/
2 ቢቢሲ አማርኛ(ታህሳስ 23)፡www.bbc.com/amharic, /ሰኔ 13/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/
3 ኤፍቢሲ(ጥር 27)፡ www.fanabc.com , /ሰኔ 13/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/

# መደወላቡ ዩኒቨርሲቲ




መደወላቡ የኒቨርሲቲ

በሕዳር ወር የወልዲያ ዩንኒቨርስቲ ክስተት ተከትሎ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ከፍተኛ ስጋትና ውጥረት ነበር። ስጋቱ ቀጥሎ ከአማራ ክልልና ከኦሮሚያ ክልል በሔዱ ተማሪዎች መካከል በመደወላቡ ዩኒቨርሲቲ ግጭት ተፈጥሮ እንደነበር የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት አቡበከር ከድር (ዶ/ር) ለቢቢሲ አማርኛ ገልጸዋል።

## የደረሱ ጉዳቶች

- 9 የሚሆኑ ተማሪዎች ላይ ጉዳት ደርሷል

## ቀጣይ ሁኔታዎች

*"ችግራችን እስካሁን አልተፈታም በማናውቀው እየተንገላታን አንገኛለን። የምናድረው በመማሪያ ክፍሎች ውስጥ ነው በመከላከያ እየተጠበቅን ነው፤ በማኅበራዊ ሚዲያዎች የማስፈራሪያ መልዕክቶች ይሰራጫሉ። እስከመቼ እንዲህ እንደምንቀጥል አልገባንም የመንግሥት ዝምታም ግራ አጋብቶናል"* ያሉት የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች፣ ግጭቱን የሚፈጥሩት እነማን እንደሆኑ ግምታቸውን ሲያስቀምጡ ደግሞ *"እንደኛ ጥርጣሬ ይህን የሚያደርጉት ተማሪዎች አይመስሉንም፤ በተመሳሳይ መታወቂያ ከውጪ የሚገቡ ናቸው"* ብለዋል። በተጨማሪም በሕዳር 15 ትምህርት እንዲጀምሩ ዩኒቨርሲቲው ጥሪ አቅርቦ ነበር።[1] ነገር ግን በሕዳር ወር ግጭት የታየባቸው ዩኒቨርሲቲዎች እነዚህ ብቻ አይደሉም። በቂ መረጃ ማግኘት አልተቻለም እንጂ የሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች አለመረጋጋት ተፅዕኖ ያሳደረባቸውና አለመረጋጋት የታየባቸው ሌሎች ዩኒቨርሲቲዎችም ነበሩ። አጠቃላይ ሁኔታቸው ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል።

1 ቲክቫህ(ሕዳር 13, /ሰኔ 13/2012 ዓ.ም ተነበኘ/

# ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ




ሀሮማያ የኒቨርሲቲ

በሕዳር ወር በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የትምህርት ስርዓት ተስተጓጉሏል ሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ለጉዳዩ ትኩረት ነፍጎታል ሲሉም ተማሪዎች አማረው ነበር። በወቅቱ ከተፈጠረው አለመረጋጋት ጋር በተያያዘ ቁጥራቸው ቀላል የማይባል ተማሪዎች ወደ አቅራቢያ ከተሞች መሔዳቸውንና ራቅ ባሉ ከተሞች የሚገኙ ተማሪዎች ደግሞ የመንገድ ደኅንነት አስተማማኝ ባለመሆኑ እዛው ለመሆን መገደዳቸውንም ጨምረው ገልጸዋል። ተማሪዎች በሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች እንደሚደረገው በበራሪ ወረቀትና በማኅበራዊ ሚዲያ የሚሰራጩ ማስፈራሪያ የያዙ መልዕክቶች እንዳይመዘገቡ ስጋት እንደሆነባቸው ገልጸው ነበር።[1]

1 ቲክቫህ ዳሰሳ(ሕዳር 12), /ሰኔ 13/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/

# ባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ






ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ

በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በሚናፈሱ ወሬዎች የግጭት ስጋት ያደረባቸው ተማሪዎች ግቢውን ለቀው ወጥተው ነበር። ወደ ቤተሰቦቻቸውም የሔዱ አንዳንድ ተማሪዎች ነበሩ። በጥር 14 ቀን በወጣ ዘገባ ደግሞ ባለፉት ሳምንታት ተማሪዎች በሚያነሷቸው ጥያቄዎች ዙሪያ ተደጋጋሚ ውይይትና ምክክር ቢደረግም ምክንያታዊ ባልሆነ መንገድ በፖሊ፣ ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ፣ ፔዳና ይባብ ግቢዎች ትምህርት ተቋርጦ ነበር ተብሏል። ዘገባው በወጣበት ቀን ግን ትምህርት ሙሉ በሙሉ መጀመሩን አሳውቀዋል።[1]

## የእርምት እርምጃ

በጥር 14 ቀን ዩኒቨርሲቲው በወሰደው እርምጃ፡-

- 4 ተማሪዎች ሙሉ በሙሉ ታግደዋል
- በ21 ተማሪዎች ላይ ደግሞ ከአንድ ዓመት እገዳ ጀምሮ እርምጃ መወሰዱን ገልጸዋል[2]

1 ፋና(ጥር 14) www.fanabc.com, /ሰኔ 15/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/
2 ibid

# ኦዳ ቡልቱ ዩኒቨርሲቲ

በተመሳሳይ በተፈጠረው አለመረጋጋት ተማሪዎች 'ችግራችን ሳይፈታ ዛሬም ሜዳ ላይ ነን፤ መንግሥት ምን እስከምንሆን እንደሚጠብቅ አልገባንም ችግራችንን ይፍታልን። ወደ ቤተሰቦቻችን ሸኙን ጥያቄም መልስ ይስጠን' በማለት የነበሩበትን ሁኔታ አስረድተዋል።[1]

# አርሲ ዩኒቨርሲቲ

በአርሲ ዩኒቨርሲቲ የነበሩ ውጥረቶች እንዳልረገቡና አሁንም ተማሪዎች ስጋት ላይ መሆናቸውን ገልጸው ነበር። መንግሥት ይህን ጉዳይ ለመፍታት እና ሰላማዊ የመማርና ማስተማር ሒደት ለመፍጠር የሚያደርገው ጥረት ደካማ ነው ሲሉም ወቅሰዋል።[2]

1 Ibid
2 Ibid

# ደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ

የደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በበኩላቸው ግቢው ውስጥ የጎላ ችግር ባይኖርም ዩኒቨርሲቲው አካባቢ 1 ተማሪ በተመሳሳይ የወልዲያን ዩኒቨርሲቲን ሁኔታ ተከትሎ በተፈጠረ ሁኔታ ከሞተ በኋላ ችግር ይፈጠራል በሚል ስጋት በርካታ ተማሪዎች ግቢውን ለቀው መውጣታቸውን ገልጸው ነበር።

በተመሳሳይ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ፣ ደባርቅ ዩኒቨርሲቲ (2 ተማሪዎች ቆስለዋል[1])፣መቅደላ አምባ እና አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ከፍተኛ ውጥረት የሰፈነባቸው ሲሆን፥ በዚሁ ሳቢያ ትምህርት ለቀናቶች ተስተጓጉሎ ነበር።[2]

የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ዲኤታ ሳሙኤል ክፍሌ (ዶ/ር) በጥቅምት መጨረሻ እና ሕዳር መጨረሻ ላይ እነዚህ ችግሮች በመከሰታቸው ምክንያት በዩኒቨርሲቲዎች ትምህርት መስተጓጎሉን አስመልክቶ በሕዳር 10 ቀን ከፋና ጋር ባደረጉት ቆይታ ችግር ተከስቶባቸው ከነበሩ ዩኒቨርሲቲዎች መካከል ወልዲያ፣ ወለጋ፣ አምቦ እና አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ በወቅቱ መረጋጋት ላይ መሆናቸውን ጠቅሰው የፀጥታ መሻሻል ባልታየባቸውና ወደ መደበኛ እንቅስቃሴ በማይገቡ ዩኒቨርሲቲዎች ላይ በተለይ ኦዳ ቡልቱ እና መቱ ዩኒቨርሲቲ ወደ ሥራ ካልገቡ እርምጃ እንደሚወስዱ ጠቅሰው ነበር። የመማር ማስተማሩ ሒደት እንዲስተጓጎል ተማሪን ከተማሪ በማጋጨት፣ ምግብ በመከልከል፣ ትምህርታቸውን እንዳይከታተሉ በማድረግና በሌሎች መሰል ድርጊቶች የተጠረጠሩ ተማሪዎችና ተማሪ ያልሆኑ ግለሰቦች በቁጥጥር ሥር ውለዋል ብለዋል። ቁጥራቸው ወደ 100 የሚደርሱ ተማሪዎች እንዲሁም ተማሪ ሳይሆኑ የዩኒቨርሲቲ መታወቂያ፣ የተለያዩ ሰነዶች፣ በርካታ የባንክ ደብተሮችና ሌሎች መረጃዎች የያዙ ግለሰቦችም በቁጥጥር ሥር ውለዋል ብለዋል። ማጣራት ተደርጎ አስተዳደራዊና እርምጃ እንደሚወሰድባቸውና በወንጀል ተጠያቂ እንደሚደረጉ አስረድተው ነበር። የዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንቶች፣ መምህራን እና የአስተዳደር ሠራተኞች በድርጊቱ ተሳትፎ ነበራቸው ብለዋል።

በሕዳር 3 ቀን የሳይንስና ትምህርት ሚኒስቴር ባወጣው መግለጫ "ሁኔታው ከመንግሥት ቁጥጥር ውጪ ባለመሆኑ ዛሬ ምሽት ተማሪዎቹ ዩኒቨርሲቲያቸው ይመለሳሉ" ብሎ ነበር። ነገር ግን ተማሪዎች አለመመለሳቸውንና በየመጠለያውና መሆናቸውን፣ ከግቢ እንዳይወጡ ግቢ ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ደግሞ በፀጥታ አስከባሪዎች ጥበቃ መሆናቸውን እና በአንዳንድ ዩኒቨርሲቲዎች ላይ ደግሞ ከግቢ እንዳይወጡ በመደረጋቸው ምክንያት ወደ ቤተሰቦቻቸው ሳይሔዱ በስጋት ያሉ መኖራቸውን ገልጸዋል።[3]

1 ዶቸ ቬለ(ሕዳር 8) ፡ www.facebook.com/dw.amharic, /ሰኔ 15/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/
2 ibid
3 ቲክቫህ (ሕዳር 4), /ሰኔ 15/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/

# ታኅሣሥ

ይህ ወር የሳይንስ እና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር የ45 የኢትዮጵያ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተማሪዎች በቅጥር ግቢያቸው እና ከቅጥር ግቢያቸው ውጪ አደጋዎች እየገጠሟቸው በመሆኑ የመንቀሳቀሻ ሰዓታቸውን የገደበበት ነበር። ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ለ45ቱ ዩኒቨርሲቲዎች በታኅሣሥ 15 ቀን በፃፈው ደብዳቤ ተማሪዎች ከንጋት 12 ሰዓት በፊትና ከምሽቱ 1 ሰዓት በኋላ ከቅጥር ግቢዎቻቸው ውጪ እንዳይገኙ ትዕዛዝ አስተላልፏል። ተማሪዎች ከምሽቱ 4 ሰዓት በኋላ ከመኝታ ክፍሎቻቸው ውጪ መቆየት እንደማይችሉ ውሳኔ አስተላልፏል።

# አምቦ ዩኒቨርሲቲ




አምቦ ዩኒቨርሲቲ

በአምቦ ዩኒቨርሲቲ በታኅሣሥ 11 ቀን 2012 ዓ.ም በዋናው ግቢ የተፈጠረውን ሁኔታ መንስዔና ያስከተለው ጉዳት አስመልክቶ የተለያዩ መረጃ ተሰጥተውበታል። የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ታደሠ ቀነዓ (ዶ/ር) እንደገለጹት በግቢው ውስጥ በተማሪዎች መካከል የነበረው ድንጋይ መወራወር

*"በተማሪዎች መካከል ግጭት እንዲቀሰቀስ የሚፈልጉ ከሌላ ዩኒቨርሲቲ የመጡ ተማሪዎች" ያነሳሱትና "የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች የሆኑ ጥቂት ተማሪዎች ከሌላ ዩኒቨርሲቲ መጡ የተባሉ ተማሪዎችን አጋርነት ለማሳየት በሚል ግጭት ለመፍጠር ሲሞክሩ"* የተፈጠረ ነው።

በግጭቱም የደረሰ የአካል ጉዳት የለም፣ ለጊዜው የመማር ማስተማር ሒደቱ ተቋርጦ ነበር ነገር ግን ግቢውን የሚያስለቅቅ የጎላ ችግር ባለመኖሩ ግቢውን ለቆ የወጣ ተማሪ የለም ብለዋል።[1]

ነገር ግን የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ከግቢው የወጡ ተማሪዎች የሉም ይበሉ እንጂ አንዳንድ ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲው ባለው አስጊ ሁኔታ ቁጥራቸው ቀላል የማይባል ተማሪዎች ግቢውን ለቀው ወጥተዋል ብለዋል። ወደ አዲስ አበባም በመምጣት በቅዱስ ራጉኤልና በሌሎች በርካታ አብያተ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሙቶዎች የሚቆጠሩ ተማሪዎችም ተጠልለው ይገኛሉ ብለው ነበር።[2] በወቅቱ ከ200 በላይ ተማሪዎች በአዲስ አበባ ቤተክርስቲያን ተጠልለው እንዳየ አንድ ጋዜጠኛ ምስክርነቱን ጽፎ ነበር።[3]

1 DW(ታህሳስ 13): https://www.facebook.com/dw.amharic/posts/3006196939413382, /ሰኔ 16/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/
2 አባይ ሚዲያ(ታህሳስ 14): http://amharic.abbaymedia.info/archives/48248, /ሰኔ 16/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/
3 ኤልያስ መሰረት ቴሌግራም ቻናል (ታህሳስ 13), /ሰኔ 16/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/

# ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ

በሕዳር ወር በዩኒቨርሲቲው ካጋጠመው የተማሪ ከፎቅ ተወርውሮ መሞት ክስተት በመቀጠል ይህ 2ኛው ነው። በታኅሣሥ 18 ቀን ከድሬዳዋ የኒቨርሲቲ ግቢም አልፎ ወደ አካባቢው መኖሪያ ቤቶችም የተዳረሰ ችግር አጋጥሞ ነበር። የዩኒቨርሲቲው 3ኛ ዓመት ተማሪ ከፎቅ ላይ በሰዎች ተወርውሮ መሞቱ ከተረጋገጠ በኋላ ዩኒቨርሲቲው ውስጥ ግጭት ተከስቶ ከግቢው ውጪም ተሸጋግሮ በአካባቢው መኖሪያ ቤቶች ላይ ድንጋይ ሲወረወር ነበር። አንድ የዩኒቨርሲቲው መምህር ለዶቼ ቬሌ መንስዔ ሊሆን ይችላል የሚሉትን ሲናገሩ ከዚህም በፊት በዩኒቨርሲቲው ግቢ በብሔር በተነሳ ግጭት ተመሳሳይ ድርጊት ተፈፅሞ አንድ ተማሪ የሞተ መሆኑን በማስታወስ ድርጊቱ ከዚያ ጋር የተገናኘ ሊሆን እንደሚችል ግምታቸውን አስቀምጠዋል። እንደሳቸው አስተያየት ከሆነ ምክንያቱ የብሔር ግጭት ሊሆን እንደሚችል ነው። ሟች መማሪያ ክፍል አካባቢ ከተደበደበ በኋላ ተወርውሮ ወደቆ ተገኝቷል። ሟች ተማሪ ከመሞቱ በፊት ድብደባ እንደ ደረሰሰበትና በሰዎች ተገፍትሮ ከፎቅ ላይ መውደቁን ደግሞ ቲክቫህ አገኘሁ ያለውን መረጃ ጠቅሶበታል።

የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር አባያ ደገፋ በቀደመው ወር አንድ የግቢው ተማሪ ከፎቅ ላይ ተወርውሮ መሞቱን አውስተው፣ በባለፉት ሳምንታትም በተማሪዎች መካከል ግጭቶች እንደነበሩና ስለት እስከመጠቀም ድረስ የከፋ ደረጃ ተደርሶ እንደነበርም አስረድተዋል። ግድያው የተፈፀመበት ተማሪ በዩኒቨርሲቲው ግቢ ብሎክ 29 አካባቢ ጉዳት ደርሶበት መገኘቱን የተመለከቱ ተማሪዎች ከፖሊስ ጋር ግጭት ውስጥ ገብተው እንደነበርና ሁኔታውንም ለመቆጣጠር አዳጋች ሆኖ ከግቢውም አልፎ የሔደ እንደነበር በወቅቱ በግቢው ውስጥ ተመልክቻለሁ በማለት ለቢቢሲ ተናግረዋል።

ከዚህ በፊት በነበሩ ግጭቶች ጉዳት የደረሰባቸውን ንብረቶች በመጠገን ላይ እንደነበሩና ተማሪዎችንም ተመልሰው ትምህርት እንዲጀምሩ ባደረጉበት ወቅት ይህ ነገር በድጋሚ መፈጠሩና አሁንም ወደቤተሰባቸው እንዲመለሱ መደረጉ ምን ያህል አሳሳቢ ሁኔታ ውስጥ እንዳሉ አመላካች ነው ብለዋል።

## የደረሱ ጉዳቶች

- የ1 ተማሪ ሞት
- ቁጥራቸው ያልተገለጸ ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸው ተማሪዎች
- የትምህርት ስርዓቱ መቋረጥ

1 DW(ታህሳስ 13): https://www.facebook.com/dw.amharic/posts/3006196939413382, /ሰኔ 16/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/
2 አባይ ሚዲያ(ታህሳስ 14): http://amharic.abbaymedia.info/archives/48248, /ሰኔ 16/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/
3 ኤልያስ መሰረት ቴሌግራም ቻናል (ታህሳስ 13), /ሰኔ 16/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/

# ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ

## ቀጣይ ሁኔታዎች

ታኅሣሥ 20 ቀን ትምህርት ተቋርጦ ተማሪዎች ወደ የቤተሰቦቻቸው እንዲመለሱ ተደርጓል። ዩኒቨርሲቲው የአደጋ ጊዜ ዕቅዶችንም ጨምሮ በግቢው ውስጥ በተማሪዎች መመገቢያ አዳራሽ፣ መኝታ ቤት እና መመሪያ ክፍሎች አካባቢ ያሉ ችግሮች ላይ የተለያዩ የለውጥ ሥራዎችን እያከናወነ እንደሚገኝ አሳውቆ ነበር።[1] ጥር 14 ቀን ትምህርት ለመጀመር ተማሪዎችን መቀበል ጀምሮ ነበር።

## የእርምት እርምጃ

በ3 የተለያዩ ወቅቶች የእርምት እርምጃ ተወስደዋል።

- ታኅሣሥ 27
    - 2 ተማሪዎች ሙሉ በሙሉ ከትምህርታቸው ተሰናብተዋል
    - 7 ተማሪዎች እያንዳንዳቸው ለሦስት ዓመት ታግደዋል
    - 8 ተማሪዎች ለ2 ዓመታት ከትምህርታቸው እንዲታገዱ
    - ከዩኒቨርሲቲው ተባርሮ የነበረ አንድ ተማሪ ተመልሶ በተፈጠረው ችግር ውስጥ ተሣትፎ በመገኘቱ በሕግ ተጠያቂ ለማድረግ ክስ እንዲመሠረትበት፣
    - ከዚህ በተጨማሪ 69 ተማሪዎች እና ተሳታፊ በነበሩ ዩኒቨርሲቲው ሠራተኞች የፈጠሩት የዲሲፕሊን ችግር ተጣርቶ በሒደት እንደ ጥፋታቸው እርምጃ እንዲወሰድባቸው ተወስኗል።[2]
- ጥር 3
    - 17 የዩኒቨርሲቲው የአስተዳደር ሠራተኞች ከሥራ ተሰናብተዋል
    - 1 ሠራተኛ ከሥራ ደረጃ ዝቅ ብሎ እንዲሠራ ተወስኗል
- ጥር 6
    - 42 ተማሪዎች እያንዳንዳቸው የመጨረሻ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል
    - 7 ተማሪዎች ለአንድ ዓመት ከትምህርት ታግደዋል
    - 2 ተማሪዎች ለ2 ዓመታት ከትምህርት ታግደዋል
    - ዩኒቨርሲቲው እስካሁን በአጠቃላይ የሥነ ምግባር ችግር በታየባቸው 68 ተማሪዎች ላይ እንደ ጥፋታቸው መጠን የቅጣት ውሳኔ ማሳለፉን ከዩኒቨርሲቲው ያገኘነው መረጃ ያመላክታል[3]
    - የደኅንነት ካሜራ በግቢው ውስጥ ተገጥሞ በተጨማሪም ወደ ግቢው የሚገባ ተማሪም ሆነ ሠራተኛ መሆኑን የሚለይ ሲስተም ተሰርቶ ጥቀም ላይ መዋሉን አሳውቀዋል[4]

1 ቲክቫህ፡ (ታህሳስ 30), /ሰኔ 16/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/
2 የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ኤጀንሲ www.ena.et, (ታህሳስ 27) /ሰኔ 16/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/
3 ፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት(ጥር 7) www.fanabc.com ,/ሰኔ 17/2012 ዓ.ም ተጎበኘ
4 ቲክቫህ (ጥር 13), /ሰኔ 17/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/ /

# አምቦ ዩኒቨርሲቲ




አምቦ ዩኒቨርሲቲ መግቢያ

የታኅሣሥ 18ቱን የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ክስተት ተከትሎ በአምቦ ዩኒቨርሲቲ አዋሮ ግቢ በታኅሣሥ 20 ቀን ግጭት ተፈጥሮ ነበር። ግጭቱ በተማሪዎችና በፀጥታ ኃይሎች መካከል የተፈጠረ ነበር። በግቢው ውስጥ የነበረውን አለመረጋጋት ለመቆጣጠር የመጡ የፀጥታ አካላት ወደ ዶርም በመግባት እርምጃ ወስደዋል ተብሏል።[1]

## የደረሱ ጉዳቶች

- 10 ተማሪዎች ቀላል እና ከባድ ጉዳት ደርሶባቸዋል
- 3 የፀጥታ አካላት ጉዳት ደርሶባቸዋል

1 ቪኦኤ (ታህሳስ 21): amharic.voanews.com: /ሰኔ 17/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/

# ወሎ ዩኒቨርሲቲ

ታኅሣሥ 23 ቀን ወሎ ዩኒቨርሲቲ ከሕዳሩ ግጭት በኋላ በድጋሚ ሌላ ችግር አስተናግዷል። ግጭቱ ምሽት አካባቢ በተማሪዎች የመመገቢያ ካፍቴሪያ የተፈጠረ ነበር። ይህ ከመፈጠሩ አስቀድሞ በታኅሣሥ 18 ቀን በተማሪዎች መካከል ተፈጥሮ የነበረው ግጭት በዕርቅ መፈታቱ ተገልጿል።

የወሎ ዩኒቨርሲቲ የአስተዳደር እና የተማሪዎች አገልግሎት ምክትል ኃላፊ አማረ ምትኩ (ዶ/ር) የአንድ ተማሪ ሕይወት የቀጠፈው ግጭት “በምን እንደተፈጠረና መንስዔው ምን እንደሆነ” እንደማይታወቅ ለዶይቼ ቬለ ተናግረዋል። በብሔር ልዩነት ተቀሰቀሰ በተባለው ግጭት የድንጋይ መወራወር ጭምር እንደነበር ዶይቼ ቬለ በዩኒቨርሲቲው ከሚገኙ ተማሪዎች ለመረዳት ችሏል።[1]

## የደረሱ ጉዳቶች

- የ1 ተማሪ ሞት
- የ1 የጥበቃ ሠራተኛ እና 1 የኮንስትራክሽን ሠራተኛ ከባድ የአካል ጉዳት ደርሷል።

## የእርምት እርምጃ

በዩኒቨርሲቲው ውስጥና ውጭ ሁከትና ብጥብጥ እንዲፈጠር ምክንያት ሆነው መገኘታቸው በማስረጃ ተረጋግጧል በተባሉ አጠቃላይ 335 ተማሪዎች፣ የአስተዳደር ሠራተኞችና መምህር ላይ እርምጃ ተወስዷል።

- 320 ተማሪዎች የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል
- 12 ተማሪዎችና ሁለት የአስተዳደር ሠራተኞች በሕግ ቁጥጥር ሥር ውለው ጉዳያቸው እየታየ ይገኛል
- አንድ መምህር ከሥራ ታግዷል

ፕሬዚዳንቱ በዩኒቨርሲቲው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በብሔርና በኃይማኖት ሽፋን በተፈጠረ አለመረጋጋት የመማር ማስተማር ስራው ባለፉት ወራት ውስጥ ለሶስት ጊዜ መቋረጡን አስታውሰዋል።[2]

1 ዶቸ ቬለ(ታህሳስ 23) Amharic: www.facebook.com/dw.amharic/photos /ሰኔ18/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/

2 ፋና ብሮድካስቲን ኮርፖሬት (ታህሳስ 29) https://www.fanabc.com/ወሎ-ዩኒቨርሲቲ-በ335-ተማሪዎች፣የአስተዳደ/,/ሰኔ 18/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/

# ሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ

በታኅሣሥ 30 ቀን በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ ግጭት ተፈጥሮ ነበር።
የሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ለዶቼ ቬይሌ በስልክ በሰጡት ቃለ ምልልስ በዕለቱ የተፈጠረውን ሁኔታ ሲገልጹ “ቀድሞውንም በዩኒቨርሲቲው የመማር ማስተማር ሒደት ተስተጓጉሎ ነበር፤ ያልተፈቱ ችግሮች ነበሩ ተማሪዎች ጥያቄዎች አላቸው። የተወሰነው ጥያቄ ከብሔር ጋር የተገናኘ ነው” ብለዋል።[1] ቢቢሲ አማርኛ ደግሞ በምዕራብ ኦሮሚያ ያለውን ችግር በመቃወም በዩኒቨርሲቲው የተነሳ ግጭት እንደሆነ ዘግቧል። ”ይህንንን ተቃውሞ ለማሰማት በግቢው ውስጥ ሰልፍ ለማድረግ ነበር ተማሪዎቹ የተሰበሰቡት፣ ከግቢው ዕውቅና ያልተሰጠው ግጭት ለማስነሳት የተደረገ ሰልፍ ነው በማለት የፀጥታ ኃይል ለማስቆም እርምጃ ወስዷል” ያሉ ሲሆን ይህ በግቢው ውስጥ ከፀጥታ ኃይሎች ጋር የተፈጠረው አለመግባባት ወደ ውጪ ወጥቶ ከተማው ላይ ያመዘነ ጥፋት እንዲፈጠር አድርጎታል ሲሉም ኃላፊው ጨምረዋል።

## የደረሱ ጉዳቶች

- ግቢው አጥር አካባቢ ያለ የደረቀ ሳር ላይ እሳት ለኩሰዋል
- የዩኒቨርሲቲው ንብረት የሆኑ 2 ሞተር ሳይክል አቃጥለዋል
- የሰርቪስ አገልግሎት የሚሰጥ መለስተኛ ተሽከርካሪ ተሰባብሯል
- በሰው ላይ ጉዳት አልደረሰም

## የእርምት እርምጃ

እርምጃ የተወሰደባቸው ተማሪዎች የመማር ማስተማር ሒደቱን ለማስተጓጎል የተለያዩ እንቅፋቶች ከመፍጠር አንስቶ በተደራጀ ሁኔታ ሠላማዊ ተማሪ ላይ ጥቃት በማድረስ፣ ሕገ ወጥ ሠልፍ በማደራጀት እና ትምህርት እንዳይካሔድ የማሸማቀቅ እና የማስፈራራት ተግባር ሲፈፅሙ ነበር ተብሏል። በተያያዘም የብሔር ግጭት የሚቀሠቅሱ ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸውን ንግግሮች ማድረግ፣ በሕገ ወጥ ሰልፍ የዩኒቨርሲቲው ንብረት ላይ ውድመት ማድረስም ተማሪዎቹ የተሳተፉበት ሕገ ወጥ ድርጊት መሆኑም ተገልጿል። በዚህም መሠረት ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ ጥፋት ፈፅመዋል ባላቸው 77 ተማሪዎች ላይ እርምጃ ወስዷል።

- 2 ተማሪዎች ከትምህርት ተሰናብተዋል
- 75 ተማሪዎች ለሁለት ዓመት ከትምህርት ታግደዋል
- 2 መምህራን ተማሪዎችን በማስኮብለል ድርጊት ላይ ተሳትፈው በመገኘታቸው የደመወዝ ቅጣትና የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል[2]

1 ዶቸ ቬለ(ታህሳስ 30) www.dw.com /ሰኔ 18/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/
2 ፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት( ጥር 1) www.facebook.com/ /ሰኔ 18/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/

# ጥር

በወርሀ ሕዳር በተለያዩ የሀገሪቱ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ግጭት የተነሳ ሲሆን የተተነሱትን ግጭቶች ያስከተሉትን ጉዳት እና የተወሰደውን እርምጃ በዚህ መልኩ አስቀምጠነዋል፡፡

# ቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ

በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ ግጭት በተነሳ በ2ኛው ቀን በቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲም ተመሳሳይ ግጭት ተነስቶ ነበር። በጥር 1 ቀን የተፈጠረው አጠቃላይ ሁኔታ ምን እንደነበር ቢቢሲ አማርኛ የዩኒቨርሲቲው የኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር ዳንኤል ሰይፉን እና አንድ የዩኒቨርሲቲውን ተማሪ ያነጋገረ ሲሆን በሁለቱም በኩል የተለያየ መረጃ ተሰጥቷል።

የዩኒቨርሲቲው የኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር አቶ ዳንኤል ሰይፉ እንደገለጹት ለተቃውሞ የወጡት ተማሪዎች በአራቱ የወለጋ ዞኖች ለምን የኢንተርኔትና ስልክ አገልግሎት ተቋረጠ፣ ለምን በኮማንድ ፖስት ሥር ሆነ የሚሉ መፈክሮችን ይዘው እንደነበርና ሰላማዊ አካሔድ እንዳልነበራቸው፣ ድንጋይ መወርወር፣ መስታወቶችን መሰባበር ላይም እንደነበሩ ገልጸዋል። *"ተማሪ ላይ አልተተኮሰም፤ ወደ ላይ ነበር ሲተኮስ የነበረው። በተማሪ ጀርባ የገባ እና በተማሪዎች ውስጥ ሆኖ የሚተኩስ አካል እንደነበር ነው የፀጥታ አካላት እየገለጹ ያሉት"* ብለዋል።

የዩኒቨርሲቲው ተማሪ እንደገለጸው ደግሞ በምዕራብ ኦሮሚያ የስልክና ኢንተርኔት መቋረጥን በመቃወም ተማሪዎቹ ጠዋት 2፡30 ሰልፍ አድርገው የነበረ ሲሆን ሰልፉም ሰላማዊ ነበር። ይሁን እንጂ በሰልፉ ላይ የነበሩ ተማሪዎችን የግቢው ፖሊሶች በዱላና በጥይት እንደመቷቸው እና በርካቶች ላይም ጉዳትም እንደደረሰ ተናግሯል። "ተተኩሶብናል፤ የግቢው ፖሊስ መሣሪያ ይዞ ባይረብሽ በሰላም ወጥተን በሰላም እንገባ ነበር"።[1]

## የደረሱ ጉዳቶች

- በፀጥታ ኃይሎች በተተኮሰ ጥይት የአንድ የ3ኛ ዓመት ተማሪ ሕይወት አልፏል
- እንደ ተማሪው መረጃ ከሆነ 8 ሰዎች በጥይት ተመተዋል፣ በርካቶች በዱላ እና በጥይት ጉዳት ደርሶባቸዋል
- የዩኒቨርሲቲው የኮሚኒኬሽን ጉዳዮ ዳይሬክተር እንዳሉት ከሆነ ደግሞ 1 ተማሪ በጥይት እግሩ ላይ ተመትቶ ወደ ሃዋሳ ሆስፒታል መላኩን አረጋግጠናል ብለዋል

1 ቢቢሲ አማርኛ(ጥር 2) www.bbc.com/amharic፡ /ሰኔ 20/2012 ዓ.ም ተነበኘ/

# ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ




ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ

በጥር ወር ሌላኛውን ግጭት ያስተናገደው ደግሞ ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ ነው። የዩኒቨርሲቲው የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አርማዬ አሰፋ ለቢቢሲ አማርኛ እንደተናገሩት በዩኒቨርስቲው ባልታወቀ ምክንያት ሱራፌል ሳሙኤል የተባለ የ1ኛ ዓመት ተማሪ አመሻሹ ላይ በተማሪዎች ዶርም ኮሪደር ላይ በስለት ተወግቶ ወድቆ መገኘቱን ገልጸዋል። በወቅቱ ደም እየፈሰሰው ስለነበር ወዲያውኑ ወደ ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል ቢወሰድም ሁኔታው አስጊ ስለነበር ሕይወቱን ማትረፍ አለመቻሉን አስታወቀዋል። ችግሩ በምን ምክንያት እንደተፈጠረ እየተጣራ እንደሆነና የተጠረጠሩ ተማሪዎችም በቁጥጥር ሥር መዋላቸውንና ሟች ተማሪ የእርሱ የዶርም ልጅ ከነበረ ተጠርጣሪ ጋር የግል ግጭት እንደነበራቸው አክለዋል።

## የደረሱ ጉዳቶች

- አንድ የ1ኛ ዓመት ተማሪ ሞትቀጣይ ሁኔታዎች

## የእርምት እርምጃ

- ግጭቱ በተፈጠረ ዕለት ተማሪዎች ከዶርም ውጪ ቆይታ ከ4 ሰዓት እንዳያልፍ
- ከንጋቱ 12፡00 ሰዓት በፊትና ከምሽት 1 ሰዓት በኋላ ከግቢ ውጪ እንዳይገኙ ውሳኔ አስተላልፎ ነበር
- የደኅንነት ካሜራ በግቢው መግቢያና መውጫ በር ላይ እንዲገጠም አድርጓል

# የካቲት

በወርሐ የካቲት ከሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር በ2012 ዓ.ም በበርካታ ዩኒቨርሲቲዎች ተቀስቅሶ የነበረውን ረብሻ ተከትሎ በዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንቶች ላይ የተለያዩ ዛቻና ማስፈራሪያዎች እየደረሱ እንደሆነ ተጠቁሟል። የሚኒስትሩ የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር አቶ ደቻሳ ጉርሙ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ ‘’የዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ሆኖ መስራት ፈታኝ እየሆነ መቷል’ ያሉ ሲሆን ግጭት በፈጠሩ ተማሪዎች ላይ እርምጃ በሚወሰድበት ቀን ‘የእገሌ ብሔር ስለሆነ ነው’ በሚል ማስፈራሪዎችን ያደርሳሉ፡ በተለይም የፀጥታ ስጋት ባላቸው አካባቢዎች ፕሬዚደንቶቹ በሚደርስባቸው ዛቻና ማስፈራሪያ ምክንያት ስጋት ውስጥ ያለነፃነት እየሰሩ እንዳሉና ተማሪዎችም ከትምህርታቸው ውጪ በሆኑ አጀንዳዎች እንዲዋጡ አድርጓል ሲሉ ተናግረዋል።[1]

# ወሎ ዩኒቨርሲቲ




ወሎ ዩኒቨርሲቲ

በየካቲት 24 ቀን በወሎ ዩኒቨርሲቲ ኮምቦልቻ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትውት ካምፓስ በሁለት ተማሪዎች መካከል የተፈጠረ ግጭት የአንድ ተማሪ ሕይወት እንዲልፍ ምክንያት ሆኖ ነበር። ፀቡ የተነሳው የተማሪዎች ዶርም ብሎክ ውስጥ በሚገኝ ፑል ቤት ከምሽቱ 1፡20 አካባቢ ነው።

የወሎ ዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት አባተ ጌታሁን (ዶ/ር) ለኢዜአ እንደገለጹት በብሔርና በሃይማኖት ሽፋን በተፈጠረ አለመረጋጋት የመማር ማስተማር ሥራው ባለፉት ወራት ውስጥ ለሦስት ጊዜ መቋረጡን አውስተዋል።[2]

1 አዲስ ዘመን(የካቲት 16)፡ /ሰኔ 20/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/
2 FBC: (ታህሳስ 280 www.facebook.com/fanabroadcasting /ሐምሌ 13/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/

# የተሰወሩት ተማሪዎች እንቆቅልሽ

ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ 8 ወራቶችን ያስቆጠረው ከደምቢ ዶሎ ዩኒቨርሲቲ ወደ ቤተሰቦቻቸው ሲመለሱ የታገቱ ተማሪዎች ጉዳይ አሁንም ድረስ መልስ ያልተገኘለት እንቆቅልሽ መሆኑን ቀጥሏል። ተገኙ የተባሉት መረጃዎችም በሌላው ቀን አወዛጋቢና አጠያያቂ ሆነው ብቅ ይላሉ። ተማሪዎቹ መቸ ታገቱ፣ አጋቾቻቸው ማን ነው፣ የተፈጠረው ሁኔታ ምንድነው፣ ቁጥራቸው ስንት ነው፣ አሁን በምን ሁኔታ ነው ያሉት እና የመሳሰሉት ተያያዥ ጥያቄዎች አሁንም መልስ አልባ ናቸው።

ሕዳር 20/21 ቀን በደምቢዶሎ ዩኒቨርሲቲ የፀጥታ ችግር በመኖሩ ምክንያት ሸሽተው ወደ ቤተሰቦቻቸው ሲመለሱ የነበሩ ተማሪዎች መታገታቸውን አስመልክቶ መረጃዎች ለሕዝብ ጆሮ ከደረሱ በኋላ ስለጉዳዩ የተጣራ መረጃ ለማግኘት እና ተማሪዎች እንዲለቀቁ የሚጠይቁ ጩኸቶች ሲስተጋቡ ነበር።

በዚህ መካከል አስመራ ሹምዬ የምትባል አንዲት ሴት"ከታገቱት ተማሪዎች መካከል አንዷ ነኝ።" በማለት በታኅሣሥ 7 ቀን ከእገታው ማምለጥ እንደቻለች ቀን ተናገረች። "መጀመሪያ በአጋቾቹ የተያዝነው 18 ተማሪዎች ነበርን። እኔ ማምለጥ ስለቻልኩ አሁን ታግተው ያሉት ተማሪዎች ቁጥር 17 ነው። ከእነዚህ መካከል 4ቱ ወንዶች ሲሆኑ 13ቱ ደግሞ ሴቶች ናቸው" በማለት በጊዜው በእገታ ላይ የሚገኙት ተማሪዎች ቁጥራቸው 17 ነው ብላለች።

በጫካው ውስጥ ለሁለት ቀናት ካደረች በኋላ፥ በሦስተኛው ቀን ወደ ዋና የመኪና መሥመር መውጣት እንደቻለችና አማርኛ በትንሹም ቢሆን መናገር የሚችሉ አባት አግኝታ ወደ ደምቢ ዶሎ ፌደራል ፖሊሶች እንደላኳት በዛም ለፌደራል ፖሊሶቹ መረጃውን ሰጥታ 'ቦታው እንኳን ለተማሪ ለወታደርም አስጊ ነው፤ እንከታተላለን' እንዳሏት ተናግራለች።[1] ቢቢሲ አማርኛ ያናገራቸው የኦሮሚያ ክልል የአስተዳደር እና ፀጥታ ቢሮ ምክትል ኃላፊ ኮሎኔል አበበ ገረሱ በምዕራብ ኦሮሚያ ስላለው ጠቅላላ ሁኔታ "ምንም ዓይነት መረጃ የለኝም። እኔ የሰማሁት ነገር የለም" ሲሉ የኦሮሚያ ኮሚኒኬሽን ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ዴሬሳ ተረፈ በበኩላቸው "ታፍኖ የተወሰደ ተማሪ የለም" ሲሉ ምላሻቸውን ሰጥተዋል።[2]

በተመሳሳይ የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ሕዝብ ግንኙነት ደቻሳ ጉሩሙ "መረጃ የለኝም" ሲሉ፣ የደንቢ ዶሎ ዩኒቨርስቲ ሕዝብ ግንኙነት ተመስገን ዓለሙ ደግሞ "እንደናንተ በወሬ ደረጃ ሰምተናል" በማለት ጉዳዩ እንደማያውቁ ሲያስረዱ ተደምጠዋል።[3]

1 አስራት ሚዲያ (ጥር 4)፡ www.youtu.be፣/ሐምሌ 12/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/
2 ቢቢሲ አማርኛ (የካቲት 24) www.bbc.com ፣/ሐምሌ 12/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/
3 ኢሳት (ታህሳስ 7)፡ www.youtu.be ፣/ሐምሌ 12/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/

# የተሰወሩት ተማሪዎች እንቆቅልሽ

የፌዴራል ፖሊስ የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት ኃላፊ ጄይላን አብዲ አስቀድሞ በጥር 8 ለአስራት ቲቪ "መግለጫ የሰጠው አካል ነው የሚያቀው፣ እኛ አናቅም። እኛ የአንዲት ሴት ጉዳይ ብቻ ነው የምናቀው"[1] ካሉ ከሳምንት በኋላ በጥር 15 ለዚሁ የቴሌቪዥን "ያለንን መረጃ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት አስገብተናል፤ የከፋ ነገር ሊኖረው ይችላል" ሲሉ ተደምጠዋል።[2]

ጉዳዩን ለማጣራት ዶቸ ቬለ ያነጋገራቸው የደምቢዶሎ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ለታ ተስፋዬ (ዶ/ር) በበኩላቸው በዩኒቨርሲቲው በተደጋጋሚ ረብሻ ይፈጠር እንደነበርና ችግሩ በተፈጠረበት ሳምንትም አለመረጋጋት መኖሩን ገልጸዋል። ይሁን እንጂ እገታውን አስመልክቶ ድርጊቱ የተፈፀመው በዩኒቨርሲቲው አካባቢ ባለመሆኑ መረጃው እንደማንኛውም ወገን እንደደረሳቸውና በዚህም ምክንያት ታግተዋል የሚለውን ለማረጋገጥ እንደማይችሉም ጭምር ገልጸዋል።በዩኒቨርሲቲው በነበረው አለመረጋጋት ምክንያት በጋምቤላ መሥመር የተጓዙ ተማሪዎች መኖራቸውን ገልጸው ነገር ግን ጉዳዩ ከነሱ ጋር በቀጥታ ይገናኝ አይገናኝ እርግጠኛ ባይሆኑም ለሚመለከተው የፀጥታ እና የከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ አካላት ማሳወቃቸውን አስረድተዋል። በዩኒቨርሲቲው በተደጋጋሚ በተፈጠረው ረብሻ ትምህርት የተስተጓጎለ ቢሆንም ከተማሪዎቹ ጋር በመነጋገር ትምህርት ለመጀመር ከሥምምነት መደረሱንም አመልክተው ነበር።[3]

የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳደር ተመስገን ጥሩነህ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ 'ባልታወቁ ኃይሎች የታገቱ ተማሪዎች እንዳሉ መረጃ እንዳላቸውና እስካሁን ከአባ ገዳዎችና ከአካባቢው ኅብረተሰብ ጋር በመወያየት ከተለቀቁት ውጪ ቁጥራቸው እስከ 4 የሚደርሱ ተማሪዎች ታግተው ይገኛሉ' ብለዋል።[4]

የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት የፕሬስ ሴክሬተርያት ኃላፊ ንጉሡ ጥላሁን ስለታገቱት ተማሪዎች በጥር 2 ቀን ለኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት(ኢቢሲ) በሰጡት ቃለ-መጠይቅ 21 ተማሪዎች መለቀቃቸውን፣ 6 ተማሪዎች (5 ተማሪዎችና 1 የአካባቢው ተማሪ ወጣት) ታግተው እንዳሉና እነሱንም እንደሚያስለቅቁ[5] ተናግረው የነበረ ቢሆንም የታጋቾች ቤተሰቦች ግን ልጆቻቸው ተለቀቁ ይባል እንጂ አላገኘናቸውም ሲሉ ቅሬታቸውን አቅርበዋል።

1 አስራት ቲሌቪዥን (ጥር 8)፡ www.facebook.com/abebaw.ambaye፣ ፣/ሐምሌ 12/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/
2 አስራት ቴሌቪዥን (ጥር 15)፡ www.youtu.be፣፣/ሐምሌ 12/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/
3 ዶቸ ቨለ(ጥር 1)፡ www.dw.com/am፣/ሐምሌ 12/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/
4 አማራ ማስ ሚዲያ ኤጀንሲ(ታህሳስ 27) www.youtu.be፣/ሐምሌ 12/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/
5 የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት (ጃን 11) www.youtu.be፣፣/ሐምሌ 12/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/

# የተሰወሩት ተማሪዎች እንቆቅልሽ

ቤተሰቦቻቸው እንደሚሉት ልጆቻቸው በኢጋቾቻቸው ስልክ እየደወሉ ያገኟቸው እንደነበር ነገር ግን የስልክ ግንኙነታቸውን ከቀናት በኋላ ማቋረጣቸውንና እስካሁንም ድረስ ተገኙ ይባል እንጂ ድምፃቸውን ሰምተው እንደማያውቁ ተናግረዋል።[1]

በሌላ በኩል የኦሮሚያ ክልል የፀጥታና ደኅንነት ም/ኃላፊ ኮለኔል አበበ ገረሱ ከመከላከያ ሠራዊት ጋር በጋራ ጥረት የታገቱት ተማሪዎች መለቀቃቸውንና ከአካላዊና መንፈሳዊ ጉዳት እንዲያገግሙ በመንግሥት እጅ እንደሚገኙ በጥር 3 ቀን ከገለጹ ከ5 ቀናት በኋላ ማለትም በጥር 8 ቀን የኦሮሚያ የመንግሥት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ኃላፊ ጌታቸው ባልቻ ተማሪዎቹ ከተለቀቁ በኋላ ወደ ዩኒቨርሲቲው መመለሳቸውን ገልጸው ነበር። እሳቸው እንደሚሉት ተማሪዎች ከእገታ በኋላ ከወላጆቻቸው ጋር ያልተገናኙት በአካባቢው የስልክ ግንኙነት አገልግሎት ባለመኖሩ ነው።

ታገቱ የተባሉትን ተማሪዎችን በተመለከተ ውይይት ለማድረግ የፌደራል መንግሥት ልዑካን ወደ ደንቢዶሎ ዩኒቨርሲቲ የተጓዙ ሲሆን በውይይቱ ወቅትም ከታገቱት ተማሪዎች መካከል 12ቱ የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች መሆናቸውን የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት አስታውቀዋል። የታገቱ ተማሪዎችን ጉዳይ በተመለከተ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን የሚመራ አጣሪ ኮሚቴ እየተከታተለው እንደሚገኝም በውይይቱ ተገልጿል።[2] የጠቅላይ ሚንስትር ጽ/ቤት የፕሬስ ሴክሬታሪያት ኃላፊ ንጉሡ ጥላሁን፣ የሳይንስ እና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስትር ዲኤታ ዶክተር ሳሙኤል ክፍሌ እና የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ጀኔራል ኮሚሽነር እንደሻው ጣሰው በጥር 20 ቀን በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት በሰጡት መግለጫ የታገቱትን ተማሪዎች ጉዳይ የሚያጣራ 3 የምርመራ ቡድን ተቋቁሞ እየሠራ እንደሆነ አስታውቀዋል።

ንጉሡ በዩኒቨርሲቲው አለመረጋጋት እንደነበርና በዚህም የተነሳ ተማሪዎች ለደኅንነታቸው በመስጋት ሲወጡ እንደነበር አውስተው፣ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ትተው እንዳይወጡና በአካባቢው ያለውን የፀጥታ ችግር ከግምት ውስጥ በማስገባት ግቢውን ጥለው ከወጡ ችግር ሊገጥማቸው እንደሚችል በመንገር ፌደራል ፖሊስ ከአካባቢው ማኅበረሰብ ጋር እንዳይወጡ ጥረት ሲያደርጉ የነበረ ቢሆንም ተማሪዎቹ ግን በማይጠበቅ መንገድ በጋምቤላ በኩል ጉዟቸውን ቀጠሉ ብለዋል። በሕዳር 25 ቀን 2012 ሱዲ በምትባል ቦታ ላይ ተማሪዎች፣ ሌሎች ወጣቶች እና አንድ የአካባቢው አመራር ጭምር መያዛቸው ተረጋግጧል ሲሉ ተናግረዋል።

1 አማራ ማስ ሚዲያ ኤጀንሲ (ጥር 4)) www.youtube.com/channel፣ ፣/ሐምሌ 12/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/

2 የኢትዮጵያ ዜ አገልግሎት(ጥር 21) https://youtu.be/2JHcRtq_JFg፡፣/ሐምሌ 12/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/

# የተሰወሩት ተማሪዎች እንቆቅልሽ

በተጨማሪም በጥር 2 ቀን 21 ተማሪዎች መለቀቃቸውን አስመልክቶ የሰጡት መረጃ ትክክለኛ እንደሆነና ተማሪዎቹ ወደ ዩኒቨርሲቲ እንደተመለሱ እንዲሁም ከ21ዱ ተማሪዎች በተጨማሪ ሌሎች ተጨማሪ ሰዎችን ማስለቀቃቸውንና 14 ተማሪዎችን ጨምሮ 5 ሌሎች ዜጎች የት እንዳለሉ እየተፈለገ ነው ብለዋል። ድርጊቱን የፈፀሙትንም ሽፍቶች ሲሉ ገልጸዋቸዋል።

መግለጫውን በሰጡበት ወቅትም 800 ተማሪዎች ዩኒቨርሲቲውን ለቀው መውጣታቸውን እንዳረጋገጡ ተናግረው ነበር። የታገቱት ተማሪዎች 17 እንደሆኑ የሚገለጸውን አስመልክቶ ደግሞ ንጉሡ ጨምረው እንዳብራሩት *"ከዩኒቨርሲቲው ያገኘነው መረጃ የሚያሳያው 12 ብቻ የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ናቸው። 5 ግን የዩኒቨርሲቲው ተማሪ ስለመሆናቸው መረጃ የለም"* ብለዋል። ተማረዎቹ የት እንዳሉ በሚመለከት በእጃቸው በቂ መረጃ እንዳላቸውና በቂ ክትትል እየተደረገበት እንደሆነ እንዲሁም ተማሪዎቹ ላይ የደረሰ ጉዳት ስለመኖሩ ማስረጃ እንደሌለ ተጠቅሷል።[1]

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በጥር 25 ቀን የታገቱ ተማሪዎች ዙሪያ ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ለተጠየቁት ጥያቄ *"...በኛ ጉዳይ እስካሁን ድረስ እገታውን ፈፅሚያለሁ ብሎ ኃላፊነት የሚወስድ ራሱን የገለጠ የተደራጀ ኃይል የለም። እነዚህ ግለሠቦች መጀመሪያ ተይዘዋል። ከዛም ተፈተዋል ከተባለ በኋላ አዳዲስ መረጃዎች መምጣት ሲጀምሩ መረጃውን ለማጥራት ሙከራ ስናደርግ ተማሪ ያልሆኑ ከተማሪ ጋር ሥማቸው የተገለፀ ሰዎች ያሉበት መሆኑ፤ ተማሪ ሆነውም አንዳንዶቹ ከተባለው ሥፍራ ውጪ መኖራቸውን የሚያመላክት መረጃ በመኖሩ፣ መከላከያም አስሶ ምንም የለም በማለቱ በመንግሥት በኩል በፍጥነት የታገቱ የሉም የሚል ድምዳሜ ወደ መውሰድ የሚያስችል ግፊቶች ነበሩ።"* ብለዋል።

*"እስካሁን ድረስ መከላከያ በስፍራው በማያደርገው ጠንካራ ኦፕሬሽን በአንድም ስፍራ የተጎዳ፣ የሞተ ሰው ልናገኝ አልቻልንም። የልጆቹን ሁኔታ አሰመልክቶ ይኼ ነው ለማለት እንደሚቸግራቸው፣ ችግር አልደረሰባቸውም አሉ እንዳይባል ልጆቹ ቤተሰብ ጋር ያልደረሱ አሉ። ሳይጎዱ እንደተጎዱ የሚነገረው እንደተጠበቀ ሆኖ ግን በውል የት እንዳሉ የማይታወቁ ግለሰቦች ደግሞ አሉ"* በማለት ያስረዳሉ።[2]

1 አማራ ማስ ሚዲያ ኤጀንሲ (ጥር 21) youtu.be ፣/ሐምሌ 13/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/
2 አዲስ ቲቪ( ጥር 25) www.facebook.com፤፣/ሐምሌ 13/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/

# የተሰወሩት ተማሪዎች እንቆቅልሽ

ግንቦት 13 እገታው ላይ የተሳተፉ 28 ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ሥር ውለው ምርመራ እየተደረገባቸው ነው ሲሉ ንጉሡ ከአሐዱ ራዲዮ ጋር በነበራቸው ቆይታ ገልጸዋል። ለችግሩ እልባት ለመስጠት መንግስት ግብረ ሀይል አቋቁሞ እየሰራ መሆኑንም አስታወቀዋል።[1] ኢጋቹ ማነው የሚለውን አስመልክቶ የተለያዩ መላ ምቶች ሲሰጡ ቆይተዋል።

በጥር 4 በምዕራብ ኦሮሚያ የሚንቀሳቀሰው የቀድሞ የኦነግ ጦር አዛዥ ዲሪባ ኩምሳ ወይም ጃል መሮ በቢቢሲ ሬዲዮ ይህንኑ አስመልክቶ ለቀረበለት ጥያቄ *"ይህን ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማሁት ከእናንተ ነው። የትግል ዓላማችን ከተማሪዎች ጋር አይገናኝም። በተማሪዎቹ ላይም ይህን የተባለውን ዓይነት ተግባር አልፈፀምንም። እንደተለመደው የእኛን ሥም ለማጉደፍ የተወራ ነው እንጂ በፍፁም እንዲህ ዓይነት ተግባር አሁንም ወደፊትም እንፈፅምም"* በማለት ለእገታው ተጠያቂ እንዳልሆኑ ተናግሯል።[2]

በኢሳት ቴሌቪዥን ተማሪዎችን አግተናቸዋል ያለ ግለሰብ በኦሮምኛ የተናገረው ትርጉም *"የታገቱት በቁሮ ነው። 18 ናቸው። 14 ቀናቸው ነው ከታገቱ። በመልካም ሁኔታ ውስጥ ናቸው"* ብሎ ነበር።[3]

በቅርቡ በሐምሌ 10 ቀን ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ከታገቱት ተማሪዎች ጋር በተያያዘ ተጠርጣሪ የሆኑ 17 ግለሰቦችን በሽብር ወንጀል ክስ እንደመሠረተባቸው ተሰምቷል። በክሱ መዝገብ መሠረት ታግተዋል ተብለው ሥም ዝርዝራቸው የቀረቡ ሰዎች ብዛት 16 ነው። እገታውም የተፈፀመው ሕዳር 24 እና 25 ነው ተብሏል።

ክስ የተመሠረተባቸው ተጠርጣሪዎቹ ሴት ተማሪዎችን አግተዋል በሚል ዐቃቤ ሕግ የእገታና የጠለፋ ሽብር ወንጀልን ጠቅሶ ነው የከሰሳቸው። ከተከሳሾቹ በአንዱ ላይ የቀረበው ክስ ደግሞ ተማሪዎቹ በጫካ ውስጥ እየተጓዙ ስለመሸባቸው ታጋቾች መሆናቸውን እያወቀ ቤቱ በማሳደሩና ሁኔታውን ለየትኛውም የመንግሥት አካል ባለማሳወቁ የሽብር ወንጀልን ባለማሳወቅ በሚል ክስ ቀርቦበታል።[4]

1 ቲክቫህ(ግንቦት 14) ፣/ሐምሌ 13/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/
2 ቢቢሲ አማርኛ(የካቲት 24) (www.bbc.com/amharic፣/ሐምሌ 13/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/
3 ኢሳት (ታህሳስ 7)፡ www.youtu.be፣/ሐምሌ 13/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/
4 የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት (ሐምሌ 10)፡ www.youtu.be፣/ሐምሌ 14/2012 ዓ.ም ተጎበኘ/

# ማጠቃለያ

ከላይ የተደረገውን አጭር ዳሰሳ በመመልከት በ2012 (ሪፖርት የተደረጉ) አጠቃላይ 28 ዩኒቨርሲቲዎች ከመጠነኛ እስከ ጉዳታቸው የከፋ የፀጥታ ችግሮችን አስተናገደው ነበር። በችግሮቹም የሰው ሕይወት ጠፍቷል፣ ከከባድ እስከ ቀላል የአካል ጉዳት ደርሷል፣ የትምህርት ስርዓቱ በከፍተኛ ሁኔታ ተስተጓጉሏል፣ በግቢው ውስጥ ተማሪዎች በስጋት ሆነው ብዙ ቀናቶችን ከግቢ ሳይወጡ በፀጥታ ኃይሎች እንዲያሳልፉ ተደርገዋል። በዶርም አካባቢ ችግር እንዳይደርስባቸው የሰጉ ተማሪዎች ደግሞ በዩኒቨርሲቲው በሚገኙ መማሪያ ክፍሎች፣ የመመገቢያ አዳራሾች ብሎም በየሜዳው እንዲያድሩ ተገደው ነበር። ግቢያቸውን ለቀው የወጡት ለሕይወታቸው አስጊ በሆነ መንገድ (በተለይም ለሴቶች) በየቤተ እምነቱ እና ያለምንም ጥበቃ በየመጠለያዎች እንዲያሳልፉ ሆነዋል።

# ማጠቃለያ

| ዩኒቨርሲቲ | የግጭቱ ጊዜ | ሞት | የሰው ጉዳት | ተጠቃሽ መነሻ |
|---|---|---|---|---|
| ወልዲያ | ጥቅምት | 2 | 13/14 | አልታወቀም |
| ደንቢ ዶሎ | ሕዳር | 1 | አልታወቀም | የወልዲያው ዩኒቨርሲቲ ግጭት |
| አምቦ | ሕዳር | | 10 | የወልዲያ ዩኒቨርሲቲ ግጭት |
| | ታኅሣሥ | | 10 | የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ግጭት |
| ወሎ | ሕዳር | 1 | 1+ | የማኅበራዊ ሚዲያ ሐሰተኛ መረጃዎች |
| | ታኅሣሥ | 1 | | አልታወቀም |
| | የካቲት | 1 | | አልታወቀም |
| ድሬዳዋ | ሕዳር | 1 | | የወልዲያ ዩኒቨርሲቲ ግጭት |
| | ታኅሣሥ | 1 | | የብሔር ግጭት |
| ደብረታቦር | ሕዳር | | 2 | የወልዲያ ዩኒቨርሲቲ ግጭት |
| ጎንደር | ሕዳር | 1 | | የወልዲያ ዩኒቨርሲቲ ግጭት |
| መደወላቡ | ሕዳር | | 9 | የወልዲያ ዩኒቨርሲቲ ግጭት |
| ደብረ ብርሃን | ሕዳር | 1 | | የወልዲያው ዩኒቨርሲቲ ግጭት |
| ቡሌ ሆራ | ጥር | 1 | 12 | አልታወቀም |
| ሐዋሳ | ጥር | 1 | | አልታወቀም |
| | | 12 | 58+ | |

ሰንጠረዥ፦ በዩኒቨርሲቲዎች በተቀሰቀሱ ግጭቶች ተማሪዎች ላይ የደረሰ ጉዳት

# ማጠቃለያ

ለዚህ ሁሉ የተማሪዎች ጉዳት የሆኑት ግጭቶች መንስዔ ምንድነው ተብሎ በሚጠየቅበት ወቅት በተጨባጭ ይህ ነው የሚል ምላሽ በአብዛኛው አይገኝላቸውም። በመግለጫው ከተደረገው ዳሰሳ መረዳት እንደሚቻለው የግጭቶቹ መንስዔ ብዙ ጊዜ የግል ወይም የሌላ ዩኒቨርሲቲ ግጭት ሆኖ፣ የሚቀጣጠለው ግን የብሔር ፅብ በመሆን ነው።

አለመረጋጋቶቹ በብዙዎች እንደሚገመቱት ተማሪዎች ብቻ የሚሳተፉበት አይደለም፣ ይልቁንም የዩኒቨርሲቲውን መምህራኖች፣ የአስተዳደር ሠራተኞች፣ ፕሮክተሮች እናም ሌሎች የችግሩ አባባሽ ይሆናሉ ተብለው የማይገመቱ አካላት እጃቸውን እንዳለበት በአንዳንድ ዩኒቨርሲቲዎች መረጋገጡአሁንም ጉዳዩ የተማሪዎች ብቻ ነው ብለን መደምደም እንደሌለብን የሚጠቁም ነው።

እርምጃ የተወሰደባቸው አንዳንድ ተማሪዎች የባንክ ደብተር ውስጥ መጠኑ ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ መገኘቱ ተገልጿል፣ ከአንድ በላይ የተለያየ ማንነት ያለው መታወቂያ ያላቸው ግለሰቦች ግቢው ውስጥ ከተማሪ ጋር ተመሳስለው ገብተው መገኘታቸውም ተገልጿል፣ ችግሮች ከመፈጠራቸው ከቀናት በፊት በአንዳንድ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ችግሮች እንደሚከሰቱ ቀድመው መታወቃቸው የመሳሰሉትንም መመልከት እንችላለን። ስለሆነም የግጭቶቹን በሚገባ ማጥናት ያስፈልጋል።

# ጥቆማዎች

ይህ መግለጫ ምንም እንኳን በዚህ ዓመት በኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ የነበሩትን ግጭቶች ጠቅላላ ምስል ከሳች ቢሆንም፥ በውሱን አቅም በመዘጋጀቱ ምክንያት በርካታ ጉድለቶች አሉበት። በዋነኝነት የዜና ምንጮችን እንደ ዋቢ አድርጎ መጠቀሙ እና በቦታቸው ተገኝቶ ተጨማሪ ምርመራ አለማድረጉ ለጉድለቱ ተጠቃሽ ነው። በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ተጨማሪ ምርምር ለማድረግ የሚፈልጉ ግን እንደ መነሻ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። መግለጫውን በማዘጋጀት ሒደት በተለያዩ አካላት ለዜና አውታሮች የተሰጡ አስተያየቶች እና ምስክርነቶች አንዳንዴ እርስ በርሳቸው የሚጋጩ በመሆናቸው እውነቱ የትኛው እንደሆነ መናገር አስቸጋሪ አድርጎታል። ነገር ግን ይህም እንደ ችግሩ አካልነት ሊታይ ይገባል። በተጨማሪም የሚከተሉት ችግሮች እርምት እንዲደረግባቸው እንጠቁማለን።

- ዩኒቨርሲቲዎች ግልጽነት የጎደላቸው መሆናቸው ችግሮቹን በቅጡ መረዳትም ሆነ መፍትሔ ማፈላለግ እንዳይቻል አድርጓል። ዩኒቨርሲቲዎች የቀውስ ጊዜ ሕዝብ ግንኙነት ሥራቸውን ለማሻሻል መሥራት ይጠበቅባቸዋል።

- በአንድ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ያሉ አመራር አካላት እርስበርስ የሚጣረሱ መረጃዎችን የሚሰጡ መሆኑ ችግሩ የተማሪዎቹ ብቻ ሳይሆን የአስተዳደር እና አካዳሚክ ሠራተኞችም ጭምር መሆኑን አመላካች ስለሆነ ሊታሰብበት ይገባል።

- የዩኒቨርሲቲዎቹ አመራር አካላት ተማሪዎቹ ደርሶብናል የሚሉትን ስጋት እና አደጋ ከመቅረፍ እና ከመከላከል ይልቅ ወደ ማስተባበል እና መካድ ያዘነበሉ መሆኑ ተማሪዎች በተቋማቸው ላይ እምነት እንዳያዳብሩ አድርጓቸዋል። ስለዚህ ተቋማቱ ለተማሪዎች ደኅንነት ተቆርቋሪነታቸውን በማረጋገጥ ያጎደሉትን እምነት መልሰው መገንባት አለባቸው።

- ማኅበራዊ ሚዲያዎች በዩኒቨርሲቲ ውስጥ የሚከሰቱ ግጭቶች በፍጥነት እንዲቀጣጠሉና እንዲዛመቱ በማድረግ ትልቁን አስተዋፅዖ እየተጫወተ የሚገኝ መሆኑን ብዙዎች ገልጸዋል። ስለሆነም፣ የመረጃ ክፍተቱን በግልጽነት መድፈን፣ የሚዲያ አረዳድ ግንዛቤን ማሳደግ እና እውነታ የማንጠር ሥራዎች ትኩረት ተሰጥቷቸው እንዲሠሩ ማድረግ ይገባል።

# ጥቆማዎች

- ብዙኀን መገናኛዎች እውነታውን በመዘገብ ለሕዝብ የመረጃ ሰጪነት ሚናቸውን በመወጣት ፈንታ ወገን ለይተው በሚደረጉ የተጠቂነት እና የወንጀይነት ፍረጃ ላይ ተሳታፊ በመሆን የችግሩ አካል ሆነው ተስተውለዋል። ግጭት አስወጋጅ አዘጋገብ ላይ ትኩረት ሰጥተው በኃላፊነት ሥሜት ክስተቶቹን እንዳሉ እንዲዘግቡ ማድረግ ያስፈልጋል።

- ዩኒቨርሲቲዎችን በፌደራል ፖሊሶች እንዲጠበቁ ማድረግ ግዚያዊ መረጋጋትን እንጂ ዘላቂ ሰላምን ሊያረጋግጥ አይችልም። የነገንም የሰላምና ደኅንነት ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያስገቡ ዘላቂ እና አስተማማኝ የመከላከል እና ግጭቶች በተከሰቱ ሰዓት ቶሎ መቆጣጠር የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል።

- ጥፋቶች ከተከሰቱ በኋላ ተመጣጣኝ እርምጃዎች እና እርምቶች እየተወሰዱ አይደለም። በሕግ አግባብ ሊፈቱ የሚገባቸው ወንጀሎች በዕርቅ ሥም እንዲታለፉ እና በተማሪዎች መካከል የቂም በቀል ሥሜት እና ቁጭት እንዲዳብር መንስዔ ሆነዋል። የእርምት እርምጃዎቹ ተመጣጣኝ መሆን ይገባቸዋል።

- ግጭቶቹ እየተደጋገሙ በመጡ ቁጥር ከፍተኛ የብዙኀን መገናኛዎች ትኩረት ሊያገኙ የሚገባቸው ቢሆንም ቅሉ፥ ያነሰ ትኩረት ሲያገኙ ተስተውሏል። ይህ ችግሮቹን ሳይሰሙ ተድበስብሰው እንዲያልፉ ከማድረጉም ባሻገር ጥቃቶችን እንደ 'ኖርማል' የመቁጠር ዝንባሌ እያስከተለ ነው። ስለሆነም ብዙኀን መገናኛዎች ያለ መሰላቸት መረጃዎችን ለሕዝብ የማድረስ ኀላፊነታቸውን መወጣት መቻል አለባቸው።

ነሐሴ, 2012

# አድራሻ


የመብቶችና ዴሞክራሲ እድገት ማዕከል
ኢሜል፡ info@cardeth.org
P.O.Box፡ 30174
www.cardeth.org
አዲስ አበባ, ኢትዮጵያ